የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ–ታህሣሥ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 19
ADDIS ABABA–31st December, 2002

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፱/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ
ደንብ ..... ገጽ ፲፱፻፸፱

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 79/2002
Council of Ministers Value Added Tax
Regulations ..... Page 1979

የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማስከፈል በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፷፬ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

ክፍል ፩
ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር ፸፱/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡–

፩· "ባለሥልጣን" ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነው ፤

፪· "የጉምሩክ ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው ፤

፫· "ሚኒስትር" እና "ሚኒስቴር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገቢዎች ሚኒስትር እና የገቢዎች ሚኒስቴር ነው ፤

፬· "አዋጅ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ ነው፤

፭· "ታክስ" ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው ።

REGULATIONS ISSUED PURSUANT TO THE VALUE ADDED TAX PROCLAMATION

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/95 (as amended) and Article 64 of the Value Added Tax Proclamation No. 285/2002.

CHAPTER 1
General

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Council of Ministers Value Added Tax Regulations No. 79/2002.

2. Definitions

In these Regulations, unless the context requires otherwise:

1) "Authority", means the Federal Inland Revenue Authority ("FIRA");
2) "Customs Authority" means the Ethiopian Customs Authority;
3) "Minister" and "Ministry" shall mean the Minister of Revenue and the Ministry of Revenue, respectively.
4) "Proclamation" means the Value Added Tax Proclamation No. 285/2002; and
5) "Tax" or "VAT" means the Value Added Tax Imposed by the Value Added Tax Proclamation.

ያንዱ ዋጋ 6.00
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫. የዕቃ አቅርቦት እና አገልግሎት መስጠት

፩. ለአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈፃፀም ለሠራተኞች የሚቀርብ ዕቃ እና የሚሰጥ አገልግሎት የሚባለው የታክሱ መሠረት የሆነውን ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ትርፋማነት ከፍ በማድረግ ሂደት ወይም እንቅስቃሴውን ለማሻሻል ለሠራተኞች የሚቀርብ እና የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን ፣ ይህ እንቅስቃሴ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ነፃ ካልተደረገ በስተቀር ታክስ የሚከፈልበት ይሆናል ።

፪. ለሠራተኞች የሚቀርብ ዕቃ እና የሚሰጥ አገልግሎት ያለክፍያ ወይም ከገበያ ዋጋ በታች በሆነ ክፍያ የተሰጠ ቢሆንም ፣ በተገቢ ክፍያ እንደተገኘ ተቆጥሮ ታክስ ይከፈልበታል ።

፫. አሠሪው በማበረታቻ መልክ ለሠራተኛው በሚያቀርበው ዕቃ እና አገልግሎት ምትክ፤

ሀ) ለሠራተኛው አስቀድሞ በጥሬ ገንዘብ የከፈለ ፣

ለ) ስለሠራተኛው ሆኖ ለአቅራቢው ክፍያ የፈፀመ ፣

ሐ) ሠራተኛው አስቀድሞ ያወጣውን ወጪ የተካለት

እንደሆነ በዚህ ዓይነት የተሰጡት ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ከታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ አቅርቦቶች ስላልሆኑ ታክስ ከፋዩ ማናቸውንም የዚህ ዓይነቱን ወጪ የታክስ ማካካሻ ሊጠይቅበት አይችልም ።

፬. አሠሪው በገዛቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ (እንደ መንገደኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ላሉ) የታክስ ማካካሻ ካላገኘ ፣ እንደዚህ ያሉትን አቅርቦቶች ለሠራተኞች የሰጠ እንደሆነ እንዲህ ያለው አቅርቦት ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ጋር የተያያዘ አቅርቦት ተደርጐ ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም ።

፭. የተመዘገበው ሰው ከታክሱ ነፃ የሆነ አገልግሎት (በኩባንያው በሚካሄድ ክሊኒክ ውስጥ የሚሰጥን የሕክምና አገልግሎት የመሳሰሉትን) የሚሰጥ ከሆነ ፣ አገልግሎቱ ታክስ አይከፈልበትም ። አሠሪው ከታክሱ ነፃ ለሆኑ አገልግሎቶች ለዋሉ ገዥዎች ለተከፈለው ታክስ በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ማካካሻ የማግኘት መብት አይኖረውም ።

፮. የዕቃው ዋጋ ክፍያ በየጊዜው በሚፈጸምበት ሽያጭ ወይም ተከራዩ በኪራዩ የውል ዘመን መጨረሻ የዕቃው ባለቤት በሚሆንበት የኪራይ ውል (በአንድነት የዱቤ ሽያጭ ውል በሚል በሚጠቀሱት) የተሸጠ ዕቃ የተመለሰ እንደሆነ የዱቤ ግዥ ፈጽሞ የነበረው ሰው ዕቃውን መልሶ ለሚረከበው ሰው በዱቤ ሽያጭ ስምምነት መሠረት ዕቃ እንዳቀረበ ይቆጠራል ። ስለሆነም የዱቤ ግዥ ፈጽሞ የነበረው ሰው የተመዘገበ ከሆነ ዕቃው የዱቤ ግዥ የፈጸመው ሰው የንግድ ሥራ ሀብት አካል ያለመሆኑ ወይም ታክስ ከሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ያለመዋሉ ካልተረጋገጠ በስተቀር በዚህ ዓይነት የቀረበው ዕቃ የዱቤ ግዥ የፈጸመውን ሰው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለማካሄድ እንደዋለ ይቆጠራል ።

፯. በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የሚሸጠው የሎተሪ ቲኬት አገልግሎት መስጠት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል ።

፰. አንድ አቅርቦት በተወሰነ መቶኛ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት እና በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት በማጣመር የያዘ በሚሆንበት ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት አንደኛው አቅርቦት ዋንኛውን አቅርቦት ለማሟላት ሲባል የሚፈጸም ካልሆነ በስተቀር እያንዳንዱ አቅርቦት ራሱን የቻለ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።

3. *Supply of Goods or Rendition of Services*

1) For purposes of Article 4, Sub-Article (3) of the Proclamation treats the supply of goods or the rendition of services to employees as supplies in the course or furtherance of a taxable activity; and therefore taxable unless the transaction is exempt under Article 8 of the Proclamation.

2) A supply of goods or services to employees are treated as supplies for consideration and therefore may be taxed, even if the employee did not pay (or paid less than market value) for the goods or services.

3) If an employer:

(a) provides an employee a cash advance,

(b) pays a supplier on behalf of the employee; or

(c) reimburses an employee

for the cost of goods or services provided as a fringe benefit, the employer is not entitled to claim any portion of the cost as a tax credit because the goods or services provided to the emplyee are not used in connection with the employer's taxable activity.

4) If an employer was denied a tax credit on the purchase of goods or services (such as a passenger vehicle), the supply of those items to an employee is not a supply in connection with a taxable activity and therefore is not subject to tax.

5) If a registered person supplies an exempt service (such as a medical service at a company-run clinic) to an employee, the service is not subject to tax and the employer is not entitled to tax credits under Article 21 of the Proclamation for tax on purchases allocable to the exempt services.

6) Where goods supplied under an installment sale or finance lease (collectively referred to as a credit agreement) are repossessed, the repossession is a supply of the goods by the debtor under the credit agreement to the person exercising the right of repossession, and where such debtor is a registered person, the supply is made in the course or furtherance of the debtor's taxable activity unless such goods did not form part of the assets held or used by the debtor in connection with that taxable activity.

7) The sale of a lottery ticket by the National Lottery Administration is a supply of services.

8) Where a supply consists both of a supply that is charged with tax at apositive rate and a supply that is charged with tax at a zero rate, each part of the supply is treated as a separate supply, unless one part is incidental to a main supply within Article 5, Sub-Article (1) of the Proclamation.

፱· በቅጥር ውል መሠረት ተቀጣሪ ለአሠሪው የሚሰጠው አገልግሎት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት አይደለም ።

፲· በአደራ ሽያጭ ውል መሠረት የሚቀርብ እና በውክልና አቋም ለሚሠራ የሚተላለፍ ዕቃ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት አይደለም ።

፲፩· በአዋጅ ቁጥር ፪፻፵፱/፲፱፻፺፫ የተዘረጋው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች ከማምረቻ መጋዘን ወጥተው ለገበያ ከዋሉ ወይም ሌሎች በአዋጁ በተዘረጋው ሥርዓት የሚሸፈኑ ዕቃዎች ለገበያ የዋሉ እንደሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደዋሉ ተደርገው ይወሰዳሉ ። ስለሆነም ዕቃዎቹ በአገር ውስጥ ገበያ ሲሸጡ በመደበኛው የማስ ከፈያ መጣኔ መሠረት ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች የሚሆኑ ሲሆን ፣ ለውጭ ገበያ ሲሸጡ በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሀ) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይች ይሆናሉ ።

፲፪· በወካዩ ስም ለሚሠራ ወኪል የሚቀርብ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለወካዩ የቀረበ ሆኖ ይቆጠራል።

፭· <u>ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፮ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለተሰጠው ትርጉም አፈፃፀም ማናቸውንም ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከመጀመር ወይም ከማቋረጥ ጋር በተያያዘ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር በዚሁ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅ ቃቄሴ ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደተከናወነ ተግባር ይቆጠራል ።

፪· ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚከተሉትን አይጨምርም ፤

ሀ) በአመዛኙ ለግል መዝናኛ ወይም ትርፍ ጊዜን ለማሳለፍ በግለሰብ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ወይም በግለሰብ ቢከናወኑ ኖሮ እንደ ግል መዝናኛ ወይም ትርፍ ጊዜን ማሳለፊያ ሆነው የሚቆጠሩ በድርጅቶች የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ፤

ለ) ከታክሱ ነፃ የተደረጉ አቅርቦቶችን ማከናወንን የሚጨምር እስከሆነ ድረስ ማናቸውም ሌላ እንቅ ስቃሴ ።

፮· <u>ዕቃዎች ወደ አገር ሲገቡ ስለሚከፈል ታክስ</u>

፩· አዋጁ በተለየ ሁኔታ እንዲፈጸም ካልወሰነ በስተቀር ፣ ዕቃዎችን ወደ አገር ስለማስገባት ፣ ስለማስተላለፍ ፣ ወደ ጠረፍ ስለማጓጓዝ ፣ የጉምሩክ ፎርማሊቲን ስለማስፈጸም፣ ስለቀረጥና ታክስ ክፍያ ፣ የተከፈለን ቀረጥ ስለመመለስ በጉምሩክ አዋጅ የተደነገጉት በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ በልዩ ሁኔታ እንዲፈጸሙ ፣ ተሻሽለው እንዲሠራ ባቸው እና ከሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣሙ የተደረጉት እንደተጠበቁ ሆነው ፣ አግባብነት እስካላቸው ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስ በሚከፈልባቸው ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

፪· ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደ አገር በሚገቡበት ጊዜ አስመጪው ለጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን ማቅረብ እና በዚሁ መሠረት ተገቢውን ታክስ መክፈል አለበት ።

፫· ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ዲክላራሲዮን ፣

ሀ) የጉምሩክ ባለሥልጣን በሚወስነው ቅፅ የተዘጋጀ ፣

ለ) ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ለማስላት የሚያስችሉ አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ፣

ሐ) የጉምሩክ ባለሥልጣን በተለይ በሚወስነው አኳኋን የሚቀርብ ፣ መሆን አለበት ።

9. The rendition of services by an employee to an employer by reason of employment is not a supply.

10. The provision of goods on consignment and the transfer of goods to a person in a representative capacity is not a supply.

11. The removal of goods from a bonded manufacturing warehouse or any supply of goods subject to an export trade duty incentive scheme under Proclamation No. 249/2001 is treated as a supply of those goods in the course or furtherance of a taxable activity in Ethiopia. If the goods are sold into the domestic market, the supply is taxable at the standard rate, and if the goods are sold for export within Article 7, sub-Article (2)(a) of the Proclamation, the supply is taxable at the zero rate.

12. a supply of goods or the rendition of services to a person as agent for a principal is treated as a supply to the principal.

4. *Taxable Activity*

1) For purposes of the definition of a taxable activity under Article 6 of the Proclamation, anything done in connection with the commencement or termination of a taxable activity is treated as carried out in the course or furtherance of that taxable activity.

2) Taxable activity does not include:

(a) an activity carried on by a natural person essentially as a private recreational pursuit or hobby or an activity carried on by a person other than a natural person which would, if carried on by a natural person, be carried on essentially as a private recreational pursuit or hobby; or

(b) an activity to the extent that the activity involves the making of exempt supplies.

5. *Tax on Imports of Goods*

1) Except where the Proclamation provides to the contrary, the provisions of the Customs Proclamation, relating to the import, transit, coastwise carriage, clearance of goods, and payment and recovery of duty, with such exceptions, modificatins, and adaptations as the Minister may by directive prescribe, shall apply, so far as relevant, to the tax charged under the Proclamation on the import of goods.

2) Where tax is payable on an import of goods, the importer shall, upon such entry, furnish the Customs Authority with an import declaration and pay the tax due on the import.

3) The import declaration shall-

(a) be in the form prescribed by the Customs Authority,

(b) state the information necessary to calculate the tax payable in respect of the import, and

(c) be furnished in the manner specified by the Customs Authority.

፬· የጉምሩክ ባለሥልጣን፣

ሀ) ስለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሆኖ ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ በአዋጁ የተጣለውን ታክስ የመሰብሰብ፣ የአስመጪውን ስም እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (ካለው)፣ ወደአገር የገቡትን ዕቃዎች የኢንቮይስ ዋጋ መያዝ እና

ለ) በፖስታ ቤቶች በኩል ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ የጉምሩክ ባለሥልጣንን ወክሎ እንዲሰበስብ ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ጋር ስምምነት ማድረግ ፣ አለበት።

፭· የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ አስመጪዎች ዕቃዎች ወደአገር በሚገቡበት ጊዜ ታክሱን ከሚከፍሉ በስተቀር በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፱/፲፱፻፺፯ የተዘረጉት ሌሎች ሥርዓቶች ተጠቃሚ የሆኑ ሌሎች አስመጪዎች ወደአገር የሚያስገቧቸው ታክስ አይከፈልባቸውም።

፮· <u>አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ</u>

፩· የዚህ ደንብ አንቀጽ (፫) ንዑስ አንቀጽ ፫ በዱቤ ሽያጭ ውል የተሸጠ ዕቃ የተመለሰ እንደሆነ የዕቃ አቅርቦት እንደሆነ እንደሚቆጠር ያመለክታል። ስለሆነም አቅርቦት ተፈፀመ የሚባለው፣

ሀ) ዕቃዎቹ ተመላሽ በተደረጉበት ቀን፣ ወይም

ለ) በዱቤ የገዛው ሰው በማናቸውም ሌላ ሕግ በዱቤ ሽያጭ ውሉ ያለበት ግዴታና መብት እንዲፀና የተደረገ ከሆነ፣ በዚህ ዓይነቱ ሕግ በዱቤ የገዛው ሰው ግዴታና መብት እንዲፀና ከተደረገበት የመጨረሻ ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን፣ ነው።

፪· የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ (ወይም ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከፊል) በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ድርጅት የተላለፈ እንደሆነ የዕቃ አቅርቦት እንደሆነ እንደሚቆጠር ያመለክታል። ስለሆነም አቅርቦቱ ተፈፀመ የሚባለው በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የመተላለፉ ተግባር ሲፈፀም ነው።

፫· የዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) በአዋጁ ቁጥር ፪፻፵፱/፲፱፻፺፯ የተዘረጋው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች የተሸጡ እንደሆነ (በአገር ውስጥ ገበያ ላይ የተሸጡትን ጭምር) በኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደዋሉ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ያመለክታል። አቅርቦቱ ተከናወነ የሚባለው ዕቃዎቹ ለአገር ውስጥ ገበያ ሲውሉ ወይም ለውጭ ገበያ ሲላኩ ይሆናል።

፯· <u>የአቅርቦት እሴት</u>

፩· ለአንድ የተለየ ደንበኛ በልዩ አስተያየት የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር ዕቃው በቀረበበት ወይም አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ በሂሳብ በታየው የዋጋ ቅናሽ ወይም የዋጋ ተመላሽ መጠን የአቅርቦቱ እሴት ሊቀንስ ይችላል። አቅርቦቱ ከተፈፀመ በኋላ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ በአዋጁ አንቀጽ ፲፫ በተደነገገው መሠረት በሂሳብ መታየት ይኖርበታል።

፪· የአቅርቦቱ ዋጋ በአዋጁ የተጣለውን እና ተለይቶ በሂሳብ ያልታየውን ታክስ የሚያካትት ከሆነ ፣ የአቅርቦቱ እሴት የሚሆነው ከዋጋው ላይ በዋጋው ውስጥ የተካተተው የታክስ መጠን ተቀንሶ ይሆናል።

4) The Customs Authority-

(a) shall collect at the time of import and on behalf of the Authority, any tax due under the Proclamation on an import of goods and, at the time, obtain the name and the taxpayer identification number, if any, of the importer, and the invoice values in respect of the import; and

(b) shall make arrangements with the Ethiopia Postal Services to perform functions on behalf of th Customs Authority in respect of tax on imports that arrive through the Postal Services.

5) Goods covered by an export trade duty incentive scheme under Proclamation No. 249/2001 are not subject to tax at the time of import, except that tax is payable upon import if the importer is covered by the duty draw-back scheme.

6) *Time of Supply*

1) Article 3, Sub-Article (6) of these Regulations, treats the repossession of goods under a credit agreement as a supply of the goods. The supply occurs:

(a) on the day that the goods are repossessed, or

(b) when the debtor may, under any law, be reinstated in his rights and obligations under the credit agreement, on the day after the last day of any period during which the debtor may under such law be so reinstated.

2) Article 4, sub–Article (9) of the Proclamation treats, as a supply of goods, the transfer of a taxable activity (or a portion of a taxable activity) as going concern. The supply occurs when the transfer under that sub-Article (9) occurs.

3) Article 3, sub-Article (8) of the Regulations, treats the removal of goods subject to an export trade duty incentive scheme under Proclamation No. 249/2001 (including a sale into the domestic market) as a supply of those goods in the course or furtherance of a taxable activity in Ethiopia. The supply of those goods occurs when the goods are supplied in the domestic market, or when the goods are exported, if they are supplied for export.

7. *Value of a Supply*

1) The value of a supply may be reduced by any price discounts or rebates allowed and accounted for at the time of the supply of goods or the rendition of services. Post-supply price adjustments must be accounted for in accordance with Article 13 of the Proclamation.

2) Where a portion of the price of a supply represents tax imposed by the Proclamation that is not accounted for separately, the value of the supply is the price reduced by an amount equal to the product of the tax.

፫· የተመዘገበ ሰው የታክስ ቅናሽ ያገኘባቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በሙሉ ወይም በከፊል ታክስ ከሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውጪ ለሌላ ተግባር ያዋላቸው እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) በዚህ ዓይነት ለተለየ ጥቅም የዋሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ታክስ በሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደዋሉ እንደሚቆጠር ያመለክታል።የገቢዎች ሚኒስትር በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ለሌላ አገልግሎት የዋሉ አቅርቦቶችን እሴት የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፬· የዕቃው ዋጋ ክፍያ በየጊዜው በሚፈፀምበት ሽያጭ ወይም ተከራዩ በኪራዩ የውል ዘመን መጨረሻ የዕቃው ባለቤት በሚሆንበት የኪራይ ውል (የዱቤ ሽያጭ ውል) የሚቀርቡ ዕቃዎች እሴት የአቅርቦቶች የጥሬ ገንዘብ እሴት ነው። በዱቤ ሽያጭ ውል የሚቀርቡ ዕቃዎች " የጥሬ ገንዘብ እሴት" ማለት የሚከተሉት ድምር ይሆናል።

ሀ) ሻጩ ወይም አከራዩ ባንክ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም በሚሆንበት ጊዜ፣

(i) ባንኩ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም ለዕቃዎች የፈፀመው ትክክለኛ ክፍያ ወይም የዕቃዎቹ የገበያ ዋጋ ከሁለቱ ከፍ ያለው፣ እና

(ii) ባንክ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም ወጪውን የሸፈነው የዕቃዎቹ የተከላ፣ የግንባታ እና የመገጣጠም ሥራ ወጪ፣ ወይም

ለ) ሻጩ ወይም አከራዩ ሌላ አቅራቢ የሆነ እንደሆነ፣

(i) አቅራቢው በመደበኛ አፈፃፀም ዕቃዎቹን እጅ በእጅ የሚሸጥበት ዋጋ፣

(ii) አቅራቢው ለተከላ፣ ለግንባታ እና ለመገጣጠም ያወጣው ወጪ፣

፭· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት በዱቤ ግዥ ውል የተገዛ ዕቃ ለሻጩ በመመለሱ በዱቤ የገዛው ዕቃ እንዳቀረበ የሚቆጠር ሲሆን፣ የአቅርቦቱ ዋጋ ዕቃው በተመለሰበት ጊዜ ተመላሽ ያልተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቀሪ ሂሳብ ይሆናል።

፮· በንዑስ አንቀጽ (፭) የተመለከተው የአቅርቦቱ ቀሪ ሂሳብ የዱቤ ገዥው በዱቤ ሽያጭ ውሉ መሠረት የከፈለው ሂሳብ ከአቀርቦቱ ዋጋ ላይ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ነው። በመሆኑም በውሉ መሠረት ተዋዋይ ወገኖች ባላቸው መብትና ግዴታ መጠን የተከፋፈለው ሂሳብ በሚያደርሳቸው ልክ የአቅርቦቱ የጥሬ ገንዘብ ዋጋ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል።

፯· የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፱/፲፱፻፺፫ተፈፃሚ የሚሆንባቸው፣

ሀ) ለውጭ ገበያ የቀረቡ፣ ወይም

ለ) በአገር ውስጥ ለሽያጭ የዋሉ ነገር ግን ወደ ውጭ ያልተላኩ ዕቃዎች ዋጋ የገበያ ዋጋ ይሆናል።

፰· በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪)(መ) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ የሚተላለፍን በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት የሚገዛ ሰው፣ ከገዛው ዕቃ ውስጥ ከፊሉን ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት ሳይሆን ለሌላ ተግባር ያዋለው እንደሆነ የዚህ ዓይነቶች አቅርቦቶች ገዥው ታክስ በሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ወይም ይህንኑ እንቅስቃሴ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንዳዋላቸው እንደሚቆጠር የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) ያደነግጋል ።

፱· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፰) የተመለከተው አቅርቦት ዋጋ ነው ተብሎ የሚወሰደው ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለመግዛት ከተፈፀመው ክፍያ ላይ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው እንዲውል ለታቀደበት ጠቅላላ ተግባር ከተከፈለው ወጪ ላይ ለዚሁ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ባልዋለው መጠን ተቀንሶ የሚቀረው ነው ።

3) If a registered person converts a portion of, or an entire good or service from use in a taxable activity to a different use and the person was allowed a tax credit in respect of the acquisition of those goods or services, Article 4, Sub-Article (2) of the Proclamation treats the change in use as a supply of the goods or services in the course or furtherance of a taxable activity. The Minister of Revenue may issue directives on the value of a supply resulting from a change in use under this Sub-Article.

4) The value of a supply of goods under an installment sale or finance lease (a credit agreement) is the cash value of the supply. The "cash value", in relation to supply of goods under a credit agreement, means -

(a) where the seller or lessor is a bank or other financial institution, an amount equal to the sum of:

(i) the consideration paid by the bank or other financial institution for the goods, or the market value of the goods, whichever is the greater, and

(ii) any consideration for erection, construction, assembly, or installation of the goods borne by the bank or other financial institution; or

(b) where the seller or lessor is a supplier, an amount equal to the sum of:

(i) the consideration for which the goods are normally sold by the supplier for cash; and

(ii) any consideration for erection, construction, assembly, or installation of the goods borne by the supplier.

5) Where the debtor is deemed to make a supply of goods under Article 3, Sub-Article (6) of the Regulations as a result of the repossession of goods under a credit agreement, the value of the supply is an amount equal to the balance of the cash value of the supply that has not been recovered at the time of the supply.

6) The balance of the cash value of the supply under sub-Article (5) is the amount remaining after deducting from the cash value so much of the sum of the payments made by the debtor under the credit agreement as, on the basis of an apportionment in accordance with the rights and obligations of the parties to such agreement, may properly be regarded as having been made in respect of the cash value of the supply.

7) The value of goods subject to an export trade duty incentive scheme under Proclamation No. 249/2001:

(a) that are removed for export, or

(b) are supplied but not exported is the market value of the goods

8) Article 4, Sub-Article (11) of the Proclamation provides that where the recipient of a zero-rated transfer of a going concern under Article 7, Sub-Article (2)(d) of the Proclamation, acquired some of the goods in that transfer for a purpose other than to make taxable transactions, the acquistion of those goods is treated as a supply of goods by the recipient in the course or furtherance of a taxable activity.

9) The value of the supply under Article 7, Sub-Article (8) of these Regulations shall be the consideration for the acquisition of the taxable activity, reduced by an amount which bears to the amount of such consideratin the same ratio as the intended use or application of the taxable activity for making taxable transactions bears to the total intended use or application of the taxable activity.

፰· *የግዴታ ወይም የፈቃደኝነት ምዝገባ እና ሥርዓቱ*

፩· የታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው የገንዘብ መጠን የሚበልጥ ወይም ሊበልጥ የሚችል መሆኑን የታክሱ ባለሥልጣን ያመነበት ቢሆንም ለሚከተሉት ምክንያቶች ታክስ ከፋዩን ከምዝገባ ነፃ ሊያደርገው ይችላል ፤

ሀ) በታክስ ከፋዩ የሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከተቋረጠ ፣ ወይም የንግድ ሥራው እንቅስቃሴ አቅም እና ስፋት በከፍተኛ ደረጃ እና በዘላቂነት እየቀነሰ ከሄደ ወይም

ለ) በታክስ ከፋዩ በሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት በጥቅም ላይ የሚውሉ የካፒታል ዕቃዎችን ለመተካት የሚውሉ የካፒታል ዕቃዎች አቅርቦት ያለ እንደሆነ ፣ ነው ።

፪· በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) ምዝገባው የፀና የሚሆንበት ቀን ተደንግጓል ። ተመዝጋቢው ምዝገባው የሚጸናበትን ቀን ሊመርጥ የሚችል ቢሆንም ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ለራሱ ምክንያቶች ምዝገባው ከሂሳብ ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ የፀና እንዲሆን ሊወስን ይችላል ።

፱· *በተናጠል ስለመመዝገብ*

፩· ለአዋጁ አፈፃፀም የተመዘገበ ሰው እና በተናጠል የተመዘገቡ የዚሁ ሰው የንግድ ሥራ ክፍሎች እንዲሁም በተናጠል የተመዘገቡ የአንድ የተመዘገበ ዋና መ/ቤት አካል የሆኑ ክፍሎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ሆነው ይቆጠራሉ ።

፪· በተናጠል የተመዘገበ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አካል በእያንዳንዱ የታክስ ዘመን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት (የአዋጁ አንቀጽ ፳፮) ። እያንዳንዱ በተናጠል የተመዘገበ የአንድ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አካል የተመዘገበ ሰው ያለበት ግዴታዎች ሁሉ የሚኖሩት ሲሆን ፣ የዋናው ድርጅት አካል እንደሆነ ይቀጥላል ።

፫· የተመዘገበ ሰው እንደ አንድ ድርጅት መመዝገቡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ እና ሌሎች የታክስ ግዴታዎችን በመፈጸም ረገድ ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትልበት ከሆነ የንግድ ሥራው አካል የሆኑ ክፍሎች በተናጠል እንዲመዘገቡለት መጠየቅ ይችላል ። የታክሱ ባለሥልጣን የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ሲቀርብለት አንድ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ እና ሌሎች የታክስ ግዴታዎችን መፈፀም በተመዘገበው ሰው ላይ በትክክል ችግር የሚያስከትሉ መሆኑን መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል ።

፬· የተመዘገበ ሰው ከንግድ ሥራ ክፍሎቹ ውስጥ ከፊሎቹ በተናጠል እንዲመዘገቡለት የጠየቀ እንደሆነ ፣ የተናጠል ምዝገባ ያልተጠየቀባቸው በዋናው ድርጅት ሥር እንደተ መዘገቡ ሆነው ይቀጥላሉ ።

፭· የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ ንዑስ አንቀጽ ፭(ሀ) የተመለከተውን ተመላሽ ሂሳብ በተናጠል ለተመዘገበው ታክስ ከፋይ ከመክፈሉ በፊት የዚሁ ታክስ ከፋይ ክፍሎች የግብር ፣ የታክስ ፣ የወለድ ወይም የመቀጫ ዕዳ የሌለባቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ።

፮· በተናጠል የተመዘገቡ ክፍሎች ለዋናው መ/ቤት ወይም አንዱ ለሌላው የሚያቀርቧቸው ዕቃዎች እና የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ለታክስ ዓላማ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል እንደተደረጉ አቅርቦቶች ይቆጠራሉ ። ስለሆነም አቅራቢው ለእነዚህ ግብይቶች የታክስ ደረሰኝ መስጠት ያለበት ሲሆን ፣ ገዥው በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ በተፈቀደው መሠረት ታክሱ እንዲቀናነስለት መጠየቅ ይችላል ።

8. *Obligatory or Voluntary Registration and Procedure*

1) The Authority may waive the requirement under Article 16 of the Proclamation to register where the Authority is satisfied that the value of a person's taxable transactions exceeds or will exceed the amount specified under Article 16, Sub-Article (1) of the Proclamaton solely as a consequence of-

(a) a cessation, or substantial and permanent reduction in the size or scale, of a taxable activity carried on by the person; or

(b) the supply of capital goods that are being replaced with other capital goods to be used in the taxable activity carried on by that person.

2) Article 18, Sub-Article (4) of the Proclamation provides for the date that registration becomes effective. While the registering person may select the date that the registration is to become effective, the Authority, in its sole discretion, may change that date to the beginning of an accounting period.

9. *Divisional Registration*

1) A registered person and its separately-registered division, and separately-registered divisions of a head office registered person, are ''related persons'' for purposes of the Proclamation.

2) A separately-registered division must file a VAT return for each accounting period (Article 26 of the Proclamation). Each separately registered part of the entity is subject to all of the obligations imposed on a registered person, but it remains a part of the entity.

3) A registered person may apply for divisional registraton if a single registration requiring a single VAT return imposes an onerous compliance burden on the registered person. The Authority, in its sole discretion, shall decide if the applicant will experience real difficulties in submitting a single VAT return.

4) A registered person may request that some, but not all divisions be registered separately, and those not registered separately treated as part of the entity's registration.

5) The Authority may withhold any refund under Article 27, Sub-Article (5)(a) of the Proclamation to a separately-registered division in order to satisfy the tax, levy, interest, or penalty payable by the entity or another division.

6) Supplies made by a separately-registered division to the head office or between separately-registered divisions are treated as supplies between related persons for tax purposes, the supplier must issue tax invoices for those transactions in accordance with the Proclamation, and the recipient can claim tax credits on the purchases to the extent provided under Article 21 of the Proclamation.

፯· የተመዘገበው ዋና መ/ቤት በተናጠል በተመዘገቡ ክፍሎች አንፃር በወጪነት የሚይዘው ሂሳብ ዋናው መ/ቤት የፈፀመው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ሆኖ ይቆጠራል ።

፰· በተመዘገበው ዋና መ/ቤት እና በተናጠል በተመዘገቡ የዚሁ አካል የሥራ ክፍሎች ወይም በሥራ ክፍሎች መካከል የሚፈፀመው ግብይት በአዋጁ አንቀጽ ፷ በተመለከተው መሠረት ተገቢ ያልሆነ የታክስ ጥቅም ለማግኘት እንዳይውል ለመከላከል የታክሱ ባለሥልጣን የቅርብ ክትትል ማድረግ አለበት ።

፱· በተናጠል የሚደረግ የሥራ ክፍሎች ምዝገባ የታክሱ ባለሥልጣን ሲፈቅድ ብቻ የሚከናወን ስለሆነ ፣ ለተናጠል ምዝገባ ብቁ ለመሆን ዋናው መ/ቤት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል ፤

ሀ) አመልካቹ በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ መሠረት በፈቃደኝነት የሚመዘገብ ሳይሆን ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆን አለበት ፤

ለ) ማመልከቻው በጽሑፍ ሆኖ ፣ የታክስ ከፋዩን መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቁጥር መያዝ አለበት ፤

ሐ) አመልካቹ የንግድ ሥራውን በድርጅት አቋም የሚያከናውነው መሆን አለበት ፤

መ) አመልካቹ ለጠቅላላ የንግድ ሥራው አንድ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቡ ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትልበት መሆኑን ማስረዳት አለበት ። አመልካቹ የተናጠል ምዝገባ ባይፈቀድ የሚያጋጥመውን ችግር እና ለጠቅላላ የንግድ ሥራው በእያንዳንዱ የሂሳብ ዘመን የተጠቃለለ የታክስ ማስታወቂያ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ የማይችልበትን ምክንያት ማስረዳት አለበት ፤

ሠ) በተናጠል እንዲመዘገብ የተጠየቀለት የንግድ ሥራው ክፍል የራሱ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ያለው መሆን አለበት ። ይህም የሥራ ክፍሉ ገቢና ወጪውን በራሱ የሚመዘገብ እና ከሌሎች የሥራ ክፍሎች የተለየ የሂሳብ መግለጫ የሚያዘጋጅ መሆንን ይጠይቃል ፤

ረ) አመልካቹ ሂሳቡን ከማጠቃለሉ በፊት እያንዳንዱ ክፍል የራሱ የሂሳብ ሥርዓት እንዲኖረው ያደረገ መሆን አለበት ፤

ሰ) በተናጠል እንዲመዘገብ የተጠየቀለት የሥራ ክፍል በንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ዓይነት እና በሚገኝበት ቦታ ተለይቶ የሚታወቅ መሆን አለበት ፤

ሸ) የእያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት እና መዝጊያው ቀን አንድ ዓይነት መሆን አለበት ።

፲· የታክሱ ባለሥልጣን የተናጠል ምዝገባውን ከማጽደቁ በፊት በዚህ ደንብ ከተዘረዘሩት ሌላ ተጨማሪ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ለመጠየቅ እና አዲስ ለሚመዘገብ ድርጅት የተለዩ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲኖሩ ሊያደርግ ይችላል ።

፲፩· የተመዘገበ ሰው ለእያንዳንዱ በተናጠል እንዲመዘገብ ለሚጠይቅበት የሥራ ክፍል የተለየ ማመልከቻ ማቅረብ እና በቅጹ ላይ የታክሱ ባለሥልጣን የሚጠይቀውን መረጃ መሙላት አለበት ። አዲስ የምዝገባ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው የምዝገባ ማመልከቻውን እና የተናጠል ምዝገባ ማመልከቻውን በአንድነት ሊያቀርብ ይችላል ።

7) Expenses allocated by the head office to a separately-registered division may be treated as taxable supplies by the head office.

8) Transactions between the head office and separately-registered divisions, or between separately-registered divisions may be closely scrutinized by the Authority to prevent the use divisional registration to obtain unintended tax benefits referred to in Article 60 of the Proclamation.

9) Separate divisional registration is discretionary with the Authroity and, to be eligible, the head office applicant must satisfy all of the following conditions:

(a) The applicant must be a registered person for VAT purposes, but not a person who voluntarily registered under Article 17 of the Proclamation;

(b) The application must be in writing and include the applicant's taxpayer identification number and VAT certificate number;

(c) The applicant must conduct its operation as an incorporated company;

(d) The applicant will experience an onerous compliance burden if it must submit a single return for its entire business operations. The applicant must describe in detail the problems likely to be encountered if divisional registration is not approved, and the reasons why a consolidated VAT return for the entire business for each accounting period cannot be submitted by the due date for each tax period;

(e) The division for which separate registration is requested must maintain an independent accounting system. This requires the division to record its receipts and payments and produce financial statements separate from its head office and/or other divisions;

(f) The applicant must already be preparing divisional accounts before consolidating them.

(g) The division for which separate registration is requested must be separately identified by reference to the nature of its activities or its location;

(h) Each division must use the same accounting period and the same year-end date as the entity.

10) The Authority may impose additional conditions before approving an application for divisional registration, or may impose different conditions on a newly-registering entity.

11) The registered person must file a separate application for each division seeking separate registration on the form and containing the information required by the Authority, or a newly-registering person must submit an applicaton for registration and an application for divisional registration at the same time.

፲፪· እያንዳንዱ በተናጠል የተመዘገበ የሥራ ክፍል የዋናው ድርጅት አካል መሆኑን የሚያሳይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት ቁጥር ይሰጠዋል ።

፲፫· እያንዳንዱ በተናጠል የተመዘገበ የሥራ ክፍል የራሱን የተለየ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት ቁጥር የያዘ የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት ።

፲፬· በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ለተመለከተው ለምዝገባ ብቁ ለሚያደርገው የገንዘብ መጠን አወሳሰን የእያንዳንዱ በተናጠል የተመዘገበ የሥራ ክፍል አቅርቦት የዋናው ድርጅት አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል ።

፲፭· የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ ፳፪(ሐ) የተፈቀደው የታክስ ማቀናነስ በእያንዳንዱ የሥራ ክፍል ሳይሆን በዋናው መ/ቤት ደረጃ እንዲከናወን ለማድረግ ይችላል ።

፲፮· የተመዘገበው ዋና መ/ቤት በተናጠል የተደረገው የአንድ የሥራ ክፍል ምዝገባ እንዲሠረዝ ሊጠይቅ ወይም የታክሱ ባለሥልጣን በራሱ አነሳሽነት የተናጠል ምዝገባው እንዲሠረዝ ማድረግ ይችላል ። ምዝገባ በሚሠረዝበት ጊዜ የሚከተሉት ደንቦች ተፈፃሚነት ይሆናሉ ፤

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን ከዚህ ያነሰ ጊዜ እንዲሆን ካልፈቀደ በስተቀር የአንድ የሥራ ክፍል የተናጠል ምዝገባ ለሁለት ዓመት የፀና ሆኖ መቆየት አለበት ፤

ለ) ማናቸውም ድርጅት ወይም በተናጠል የተመዘገበ ክፍል የተናጠል ምዝገባ በሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች መሥራቱን ያቋረጠ እንደሆነ ዋናው መ/ቤት የሁኔታዎቹ መሟላት መቀጠሉ ከተቋረጠበት ቀን አንስቶ በ፴ ቀን ጊዜ ውስጥ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት ፤

ሐ) የታክሱ ባለሥልጣን የተናጠል ምዝገባ የሚፈቅድባቸው ሁኔታዎች መሟላት መቋረጡን ያወቀ እንደሆነ ወይም ሥረዛው የታክሱን ገቢ ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ምዝገባውን ለመሠረዝ ይችላል ፤

መ) የታክሱ ባለሥልጣን የሥራ ክፍል የተናጠል ምዝገባ እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ ለማድረግ ብቸኛ ሥልጣን አለው ፤

ሠ) የሥራ ክፍል የተናጠል ምዝገባ ሥረዛ የፀና የሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን ከሚወስነው ቀን ጀምሮ ይሆናል ።

፲· *የምዝገባ መሠረዝ*

፩· የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀን ጊዜ ውስጥ ምዝገባው እንዲሠረዝ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት ።

፪· በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ምዝገባ እንዲሠረዝ የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሑፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን ፤ ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ያቋረጠበትን ቀን እና ታክስ ከፋዩ ግብይቱን ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ ባለው የ፲፪ ወር ጊዜ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለማከናወን ያቀደ መሆን ያለመሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት ።

12) Each separately-registered division will be issued a taxpayer identification number and VAT certificate number that identifies it as a division of the entity.

13) Each registered division must issue tax invoices listing its unique taxpayer identification number and VAT certficate number.

14) For purposes of the registration threshold under Article 16 of the Proclamation, the supplies of each separately-registered division are included as supplies of the entity.

15) The Authority may require the allocation of tax credits under Article 21, Sub-Article (22)(c) of the Proclamation to be made on an entity basis, rather than on a division-by-division basis.

16) The home office registered person may apply in writing for the cancellation of the separate registration of a division, or the Authority may initiate a cancellation of a divisional registration. The following rules shall apply:

(a) Unless the Authority approves a shorter period, the separate registration of a division must remain in effect for not less than two years;

(b) If an entity or a division ceases to satisfy any of the conditions imposed on divisional registration, the entity must notify the Authority in writing of the change within 30 days of the date any condition to be met;

(c) The Authority may cancel a divisional registration if the conditions are no longer satisfied or if the Authority believes that cancellation is necessary for the protection of the revenue;

(d) The Authority shall have sole discretion to determine if the divisional registration shall be allowed to continue;

(e) The cancellation of divisional registration shall be effective from the date specified by the Authority.

10. *Cancellation of Registration*

1) A registered person must apply for cancellaiton of registration within 30 days of the date the person ceases to make taxable transactions.

2) The application for cancellation under sub-Article (1) shall be in writing, shall state the date upon which the person ceased to make taxable transactions, and shall state whether or not that person intends to make taxable transactions within 12 months from that date.

፫· የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማከናወን ካቋረጠበት ቀን አንስቶ ካለው የ፲፪ ወር ጊዜ ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ያከናውናል ለማለት በቂ ምክንያት ከሌለው በስተቀር በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ምዝገባ እንዲሠረዝ የቀረበውን ማመልከቻ ማጽደቅ አለበት ።

፬· ምዝገባ የሚሠረዘው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ቢሆንም ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ምዝገባውን ካከናወነበት ቀን ጀምሮ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ያመለፈፀሙን ካረጋገጠ ፣ ወደኋላ በመመለስ ምዝገባው ከፀናበት ቀን ጀምሮ እደሠረዘ ማድረግ ይችላል ።

፭· በአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተደነገገው መሠረት ምዝገባ ሲሠረዝ ፣ የተመዘገበው ሰው በእጁ የሚገኙትን ዕቃዎች ታክስ በሚከፈልበት ግብይት እንደ ሽጣቸው ይቆጠራል ።

፮· የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብን ጨምሮ ምዘገባው የፀና በሆነበት ጊዜ ውስጥ ባከናወነው ማናቸውም ተግባር ምክንያት ታክስ ከፋዩ በአዋጁ የተጣለበት ግዴታ ወይም ኃላፊነት ምዝገባ በመሠረዙ ምክንያት የሚቋረጥ አይሆንም ።

፲፩· *የታክስ ማቀናነስ ደንቦች*

፩· ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ካልተሟሉ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የታክስ ማቀናነስ ሊደረግ አይችልም።

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ፣ ፳፫ ወይም ፲፫ መሠረት ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ የታክስ ደረሰኝ ወይም የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ሠነድ የተሰጠ እና የታክስ ማቀናነስ እንዲፈቀድለት የሚጠይቀው የተመዘገበ ሰው የታክስ ማስታወቂያ በሚያቀርብበት ጊዜ እነዚህን ደጋፊ ሠነዶች (ደረሰኝ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር) ካላቀረበ ፣

ለ) የታክስ ማቀናነስ እንዲፈቀድለት የሚጠይቀው የተመዘገበ ሰው ወደ አገር ያስገባውን ዕቃ በሚመለከት የታክስ ማስታወቂያ ሲያቀርብ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ በጉምሩክ አዋጅ መሠረት የተዘጋጀ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ወይም በጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠ ሌላ ሠነድ ካላቀረበ ፣

፪· ታክስ የሚከፈልበት ወይም ከታክሱ ነፃ የሆነውን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ለመጀመር ወይም ለማቋረጥ የወጡ ወጪዎች በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የተፈቀዱ የታክስ ተቀናሾች ስሌት በሚከናወኑበት ጊዜ ከግምት ውስጥ የሚገቡ ይሆናል ።

፫· በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሀ) ለመንገደኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች የታክስ ማቀናነስ እንደማይደረግ የተደነገገው በዋንኛነት ዕቃ ለማጓጓዝ የሚውሉ የንግድ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ወይም ሌሎች ተሽከርካዎችን አይጨምርም።

፬· ለአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ ፫(ለ) አፈፃፀም የተመዘገበ ሰው ኃላፊዎች፣ ሠራተኞች ወይም ደንበኞች በሬስቶራንት የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ ወይም ሠራተኞች ለመዝናናት ከሥራ ቦታቸው ውጪ በሚገኙበት ጊዜ ለመኝታ እና ለምግብ በሚፈፅመው ግዥ ላይ የሚከፍለው ታክስ እንዲቀናነስ አይፈቀድም። ይሁን እንጂ የተመዘገበው ሰው "የመዝናኛ አገልግሎት" በመስጠት የንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ (ለምሳሌ ሬስትራንት) ታክስ ለሚከፈልበት የመዝናኛ ንግድ ሥራ በቀጥታ እንዲውሉ በሚገዛቸው የመዝናኛ ዕቃዎች ላይ የከፈለው ታክስ እንዲቀናነስ ይደረጋል።

3) The Authority shall approve an applicaiton for the cancellation of registration under (2) unless the Authoirty has reasonable grounds to believe that the person will make taxable transactions at any time within 12 months from the date of cessation.

4) While the cancellation of registration generally takes effect on the date of cessation, if the Authoity is satisfied that the registred person did not make taxable transactions from the date the registration took effect, the Authority can cancel the registration retroactive to that effective date.

5) When registration is cancelled, to the extent provided under Article 4, Sub-Article (4) of the Proclamation, the registered person may be deemed to have sold the goods on hand in a taxable transaction.

6) Any obligation or liability under the Proclamation, including the furnishing of returns, of any person in respect of anything done by that person while the person was a registered person, is not affected by cancellation of the person's registration.

11. *Tax Credit Rules*

1. No tax credit is allowable under Article 21 of the Proclamation unless:

(a) a tax invoice, or debit or tax credit note, in relation to the supply, has been provided in accordance with Articles 22, 23, or 13 of the Proclamation and the registered person claiming the tax credit is holding that supporting document (unless an invoice is not required) at the time any return in respect of the supply is furnished; and

(b) a Customs Declaration as prescribed under the Customs Proclamation, or a document issued by the Customs Authority evidencing payment of tax in relation to an import is held by the registered person claiming the credit at the time any return in respect of the import is furnished.

2) The cost incurred to begin or terminate a taxable or exempt activity are taken into account in calculating the allowable tax credits under Article 21 of the Proclamation.

3) Article 21, Sub-Article (3)(a) of the Proclamaiton, denying a tax credit on the acquisition of a passenger vehicle, dose not apply to a commercial truck or other vehicle designed and used primarily for the carriage of goods.

4) For purposes of Article 21, Sub-Article (3)(b) of the Proclamation, a tax credit is not allowed for VAT on the purchase by a registered person of restaurant meals for executives, employees, or customers, or for VAT on the rental of a lodge and the charge for food at a retreat for employees. The disallowance rule does not apply to purchases of "entertainment" by a registered person engaged in the business of selling "entertainment" (such as a restaurant) if the purchases are used directly in the provision of taxable entertainment.

፫· የተጨማሪ እሴት ታክስ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የተመዘገበ ሰው በተመዘገበ ጊዜ በእጁ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ ታክስ እንዲቀናነስለት ሊጠይቅ የሚችለው ዕቃዎቹን የገዛው ምዝገባው ከፀናበት ቀን በፊት ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከሆነ እና እነዚህን ዕቃዎች ከምዝገባው በኋላ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያውላቸው ከሆነ ነው።

፮· የተመዘገበ ሰው በአንድ የታክስ ዘመን ውስጥ እንዲቀናነስለት ሊደረግ የሚችለው የታክስ መጠን ድምር በዚሁ የታክስ ዘመን ውስጥ ባከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ የበለጠ እንደሆነ በብልጫ የሚታየው ሂሳብ በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ ስለተመላሽ በተደነገገው መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

፲፪· በገዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ

፩· አገልግሎት ሰጪው እና ተቀባዩ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ምክንያት ወደአገር የሚገባ አገልግሎት ዋጋ የገበያ ዋጋ እንዲሆን ካልተደረገ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ መሠረት ታክስ የሚከፈልበት ወደአገር ውስጥ የሚገባ አገልግሎት ዋጋ አገልግሎት ተቀባዩ ለአገልግሎቱ መክፈል ያለበት ዋጋ ነው።

፪· በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ መሠረት ታክስ በሚከፈልበት ወደአገር ውስጥ በሚገባ አገልግሎት ላይ መክፈል ያለበት ዋጋ ተለይቶ ያልተጠየቀ ታክስን የሚጨምር ከሆነ፣ የአገልግሎቱ ዋጋ ተደርጉ የሚወሰደው በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ዋጋ ላይ የታክስ ሂሳብ ከተቀነሰ በኋላ ይሆናል።

፲፫· በወኪል አማካኝነት ስለሚከናወን ግብይት

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ወኪል ወካይ በሆነው ሰው ስም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የፈፀመ እንደሆነ እና ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ገዥ የሆነው የተመዘገበ ሰው ከሆነ ወኪሉ ለግብይቱ የታክስ ደረሰኝ መስጠት ያለበት ሲሆን፣ ወካዩ ደረሰኝ መስጠት የለበትም።

፪· ወካይ በሆነው ሰው ስም ለወኪሉ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የተፈፀመ እና ወካዩ የተመዘገበ ሰው ከሆነ፣ በወኪሉ ጥያቄ በግብይቱ ለተሳተፈው ወኪል የታክስ ደረሰኝ መሰጠት ያለበት ሲሆን፣ ከግብይቱ ጋር በተያያዘ ለወካዩ ጭምር ደረሰኝ መሰጠት የለበትም።

፲፬· የታክስ ማስታወቂያ ቅፅ እና የሚቀርብበት አኳኋን

በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ የተደነገገው የታክስ ማስታወቂያ ባለሥልጣኑ በሚወስነው ቅፅ የሚዘጋጅ ሆኖ፣

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ ፳ መሠረት በታክስ ዘመኑ ውስጥ መክፈል ያለበትን ታክስ ለማስላት የሚያስችለውን አስፈላጊ መረጃ የሚይዝ፣

ለ) ባለሥልጣኑ በሚወስነው አኳኋን የሚቀርብ መሆን አለበት።

፲፭· ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ

፩· የአዋጁ አንቀጽ ፳፯ ንዑስ አንቀጽ ፭(ለ) የተከፈለ ታክስ ከተቀናነሰ በኋላ የሚቀረው ተመላሽ ሊደረግ የሚገባ ሂሳብ ከብር ፶ ያልበለጠ ከሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ይህንን የገንዘብ መጠን ተመላሽ እንደማያደርግ ይደነግጋል። ስለሆነም ተመላሽ ሊደረግ የሚገባው ሂሳብ ብር ፶ ወይም ከዚህ በታች ከሆነ ይህ የገንዘብ መጠን ለወደፊት እንዲሸጋገር ተደርጉ በቀጣይ የሂሳብ ዘመን ሊከፈል ለሚገባው ታክስ እንዲታሰብ ይደረጋል።

5) A person who registers after VAT becomes effective can claim credit for tax on goods on hand when the registration takes effect if the goods were acquired within the six month period before the effective date, and the goods are to be used in a taxable activity carried on by the person after registration.

6) Where the total tax credits available to registered person for an accounting period exceed the total amount of tax chargeable on taxable transactions for that period, the amount of the excess is dealt with in accordance with the refund rules under Article 27 of the Proclamation.

12. *Reverse Taxation*

1) The value of an import of services taxable under Article 23 of the Proclamation generally is the amount of the consideration that the recipient is obliged to pay for the services, except that if the supplier and the recipient are related persons, the value of the import is its market value.

2) Where a portion of the consideration charged for imported services taxable under Article 23 of the Proclamation represents tax that is not accounted for separately, the value of the import is the consideration under (1), reduced by an amount equal to the tax fraction multiplied by that consideration. The tax fraction is r(100 + r), where "r" is the rate of ta x applicable under Article 7, Sub-Article (1) of the Proclamation.

13. *Transactions by Agent*

1) Where a taxable transaction has been made by an agent on behalf of the agent's principal as specified under Article 24, Sub-Article (1) of the Proclamation, and the recipient of the taxable transaction is a registered person, the agent may issue a tax invoice in accordance with the Proclamation in relation to the transaction; and the principal shall not also issue a tax invoice in relation to the taxable transaction.

2) Where a taxable transaction has been made to an agent on behalf of the agent's principal and the principal is a registered person, at the request of the agent, a tax invoice in relation to the taxable transaction may be issued to the agent; and a tax invoice shall not also be issued to the principal in relation to the taxable transaction.

14. *Form and Manner of Filing Returns.*

A return required by Article 26 of the Proclamation shall be in the form prescribed by the Authority, and shall:-

(a) state the information necessary to calculate the tax payable for the accounting period in accordance with Article 20 of the Proclamation, and

(b) be furnished in the manner prescribed by the Authority.

15. *VAT Refund*

1) Article 27, Sub-Article (5)(b) of the Proclamation provides the Authority is not obliged to refund excess credits if the amount to be refunded is not more than 50 Birr. If the amount eligible for refund is 50 Birr or less, this amount can be carried forward and credited against tax due in the subsequent accounting period.

፪· ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ጥያቄ የሚያቀርብ የተመ ዘገበ ሰው ተገቢውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን የተመዘገበው ሰው ማስታ ወቂያውን እስከሚያቀርብ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ መሠረት ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ሂሳብ ይዞ ለማቆየት ይችላል።

፫· የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ ንዑስ አንቀጽ (፮) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ሂሣብ ያልመለሰ እንደሆነ ሂሣቡ ተመላሽ ሊደረግ ከሚገባው ቀን አንስቶ እስከተመለሰበት ቀን ድረስ ላለው ጊዜ ወለድ ይከፍላል።

፲፮· ታክስ ስለመወሰን

፩· የታክሱ ባለሥልጣን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የተጨማሪ ታክስ ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፤

ሀ) ታክስ ከፋዩ የአዋጁ አንቀጽ ፳፮ በሚያዘው መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ወይም የዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ በሚያዘው መሠረት እቃዎችን ወደ አገር ያስገባበትን ዲክላራሲዮን ያላቀረበ እንደሆነ፤

ለ) ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የታክስ ማስታወቂያ ወይም እቃዎች ወደ አገር የገቡበትን ዲክላራሲዮን የታክሱ ባለሥልጣን አጥጋቢ ሆኖ ያላገኘው እንደሆነ፤

ሐ) የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገ ባውን ታክስ ያልከፈለ መሆኑን የሚያሣምን በቂ መረጃ ያገኘ እንደሆነ፤

መ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው ባቀረበው ዕቃ ወይም በሰጠው አገልግሎት ላይ ታክስ እንደተከፈለበት አድርጐ ያቀረበ እንደሆነ፤

ሠ) የተመዘገበ ሰው ያቀረበው ዕቃ ወይም የሰጠው አገልግሎት ታክስ የማይከፈልበት ግብይት ወይም በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ሆኖ ሳለ ከዜሮ በላይ በሆነ የማስከፈያ ልክ ታክስ እንደተከፈ ለበት አድርጐ ያቀረበ እንደሆነ፤

ረ) በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን ግዴታ በሚመለከት ውሣኔ የሰጠ እንደሆነ፤

፪· የግብር ውሣኔ የሚሰጠው፤

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭(መ) ወይም (ሠ) የተደነገገውን በሚመለከት አቅርቦቱን ባከናወነው ሰው ላይ፤

ለ) በንዑስ አንቀጽ ፭(ረ) የተደነገገውን በሚመለከት በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ላይ፤

ሐ) በሌሎች ሁኔታዎች በአዋጁ መሠረት ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ላይ፤ ይሆናል።

፫· የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ መሠረት ታክስ ከፋዩ በተጨማሪ እንዲከፍል የሚጠይቀውን ታክስ በግምት ሊወስን ይችላል።

፬· በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ መሠረት የተጨማሪ ታክስ ውሣኔ የተሰጠ እንደሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ለታክስ ከፋዩ የውሣኔ ማስታወቂያ ይልክለታል። ይህም የውሣኔ ማስታወቂያ፣

ሀ) ሊከፈል የሚገባውን ታክስ፣ እና

ለ) ታክሱ መከፈል የነበረበትን ቀን ጭምር የሚይዝ መሆን አለበት።

፭· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የተሰጠ የውሣኔ ማስታወቂያ ወይም የዚሁ ውሣኔ ማስታወቂያ የተረጋገጠ ቅጂ በትክክል የተሰጠ ውሣኔ እንደሆነ ተቆጥሮ በማናቸውም የክርክር መድረክ በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል።

2) Where a registered person applying for a tax refund has failed to furnish a required return, the Authority may withhold payment of any amount refundable under Article 27 of the Proclamation until the registered person furnishes such return.

3) If the Authority does not pay the refund in a timely manner as provided under Article 27, Sub-Article (6), the Authority shall pay interest calculated from the date on which the refund was due until the date on which the payment of the refund is made.

16. *Assessment of Tax*

1) The Authority may issue an additional assessment in a variety of circumstances, including the case where:
   (a) a person fails to furnish a return as required by Article 26 of the Proclamation fails to furnish an import declaration as required by Article 5 of the Regulations;
   (b) the Authority is not satisfied with a return or import declaration furnished by a person;
   (c) the Authority has reason to believe that a person has become liable for the payment of an amount of tax but has not paid such amount;
   (d) a person, other than a registered person, supplies goods or services and represents that tax is charged on the supply;
   (e) a registered person supplies goods or services and the supply is not a taxable transaction or is a taxable transaction charged with tax at the rate of zero per cent and, in either case, the registered person represents that a positive rate of tax is charged on the transaction; or
   (f) the Authority has determined the liability of any person in terms of Article 60, Sub-Article (2) of the Proclamation.

2) The person assessed:
   (a) in the case of an assessment under Sub-Article (1)(d) or (e) of this Article, is the person making the supply; or
   (b) in the case of an assessment under Sub-Article (1)(f) of this Article, is the person whose liability has been determined under Article 60, Sub-Article (2) of the Proclamation; or
   (c) in any other case, is the person required to account for the tax under the Proclamation.

3) In making an additional assessment under Article 29 of the Proclamation, the Authority may estimate the tax payable by a person.

4) Where an additional assessment has been made under Article 29 of the Proclamation, the Authority shall serve a notice of the assessment on the person assessed, which notice shall include-
   (a) the tax payable; and
   (b) the date the tax is due.

5) The production of a notice of assessment under Sub-Article (4) of this Article or a certified copy of a notice of assessment is receivable in any proceedings as conclusive evidence that the assessment has been duly made.

፮. በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የተዘጋጀ ወይም የተሰጠ የውሣኔ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ማናቸውም ሰነድ በይዘት እና በውጤት በአዋጁ የተደነገገውን የሚያሟላ እና በውሣኔ ማስታወቂያ የተጠቀሰው ወይም ማስታወቂያው እንዲሰጠው የታሰበ ሰው ግብሩ የሚፈለግበት ሰው መሆኑ ከታወቀ ሰነዱ፣

ሀ) በትክክለኛ ቅጽ ያልተዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት ሊሠረዝ ወይም የሚሠረዝ ሊሆን አይችልም፣

ለ) በሰነዱ ላይ በተፈፀመ ስህተት ወይም ጉድለት ወይም ሊካተት የሚገባው ነጥብ ያልተካተተ በመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት ሊያጣ አይችልም።

፲፯. ንብረትን ስለመያዝ

፩. በአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ታክስ ከፋይ ንብረት ከመያዙ ከ፴ ቀን በፊት ለታክስ ከፋዩ ማስታወቂያ መላክ ያለበት ቢሆንም፣ ተገቢውን ጥረት አድርጉ ማስታወቂያ ሊደርሰው የሚገባውን ሰው አድራሻ ማግኘት ያልቻለ እንደሆነ ማስታወቂያው እንደተሰጠ ተቆጥሮ ንብረቱን መያዝ ይችላል።

፪. ታክስ ከፋዩ ንብረቱን ለመያዝ ምክንያት የሆነውን የታክስ እዳ እና ንብረቱን ለመያዝ የወጣውን ወጪ የከፈለ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፴፩ መሠረት የተያዘው ንብረት ለንብረቱ ባለቤት ወይም ንብረቱ ከመያዙ በፊት ንብረቱ በጥበቃው ወይም በይዞታው ሥር ለነበረው ሰው እንዲመለስ ያደርጋል።

፲፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩. በዚህ አንቀጽ ውስጥ፡-

ሀ) "ብቁ የሆኑ እቃዎች" ማለት የካፒታል እቃዎችን ጨምሮ ወደ አገር የገቡ ወይም በአገር ውስጥ የተገዙ ዕቃዎች ናቸው፣

ለ) "የተሻረ ሕግ" ማለት የሽያጭና ኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፷፰/፹፭ ነው፣

ሐ) "የሽያጭ ታክስ" ማለት በሽያጭና ኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ የተጣለው ታክስ ነው።

፪. አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በአገር ውስጥ የተገዙ እና ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎችን በሚመለከት፣ ታክስ ስለመጣል፣ ስለመክፈል፣ ስለመወሰን፣ ሪፖርት ስለማድረግ፣ የተከፈለን ታክስ ስለማስመለስ የተደነገጉትን ጨምሮ፣ በተሻረው ሕግ ውስጥ ያሉ ድንጋጌዎች በሙሉ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

፫. በተሻረው ሕግ መሠረት የተሰጠና አዋጁ ሥራ ላይ እስከዋለበት ቀን ድረስ ፀንቶ የነበረው የውክልና ሥልጣን በአዋጁ መሠረት የተሰጠ ሥልጣን እንደሆነ ተደርጉ ይቆጠራል ።

፬. በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ (፩) የተመለከተው ቢኖርም የተመዘገበው ሰው ታክሱ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባለው የመጀመሪያ የሂሣብ ጊዜ ሊከፍል የሚገባው ታክስ ስሌት ሲከናወን ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት የሚሠላው እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት ተቀናሽ የሚደረገው የሽያጭ ታክስ መጠን በአንቀጽ ፳፩ መሠረት ተቀናሽ እንደሚደረግ ሂሣብ እንዲያዝለት ሊጠይቅ ይችላል ።

፭. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) አፈፃፀም ፣

(i) የተመዘገበው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት ባለው የሥራ ቀን መጨረሻ ታክሱ ሥራ ላይ ከዋለበት ከ፮ ወር በፊት የተገዙ ብቁ የሆኑ ዕቃዎች በእጁ የተገኙ እንደሆነ ፣ እና

6) No assessment or other document purporting to be made, issued, or executed under the Proclamation or this Regulations shall be:

(a) quashed or deemed to be void or voidable for want of form; or

(b) affected by reason of mistake, defect, or omission therein,

if it is, insubstance and effect, in conformity with the Proclamation or this Regulation and the person assessed, or intended to be assessed or affected by the document is designed in it according to common understanding.

17. *Seizure of Property*

1) While the Authority must give 30 days notice under Article 31, Sub-Article (4) of the Proclamation before seizing property of a person in default, after making reasonable enquiries, the Authority does not have sufficient information to identify the person on whom the notice should be served, the notice shall be deemed to have been served and then it shall proceed to seize the property.

2) The Authority may authorize the delivery of goods seized under Article 31, of the Proclamation to the owner of the goods or the person who had custody or control of the goods immediately before seizure, where that person pays the tax or other amount due that gave rise to the seizure.

18. *Transitional Rules*

1) In this Article:

(a) ''qualifying goods'' means an import or purchase of goods, including capital goods;

(b) ''repealed legislation'' means The Sales and Excise Tax Proclamation No. 68/93; and

(c) ''sales tax'' means the sales tax imposed under The Sales and Excise Tax Proclamation No. 68/93.

2) The repealed legislation, including the rules governing the levy, payment, assessment, reporting, and recovery of those taxes, continues to apply to a supply or import that takes place prior to the date on which the Proclamation comes into force.

3) Every appointment made under the repealed legislation and subsisting at the date of commencement of the Proclamation shall be deemed to be an appointment made under the Proclamation;

4) Notwithstanding Article 21, Sub-Article (1), of the Proclamation in calculating the amount of tax payable by a registered person in respect of the first accounting period after the tax becomes effective, the registered person may claim as an amount creditable under Article 21, an amount equal to the sales tax calculated in accordance with Sub-Article (6) of this Article and creditable under Sub-Article (7) of this Article.

5) For purposes of Sub-Article (5) of this Article,

(i) where a registered person held, at the end of the last business day prior to the date the value added tax comes into force, qualifying goods being goods acquired not more than six (6) months before the tax comes into force; and

(ii) የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ የእነዚህን ዕቃዎች ግዥ ሲፈጽም በሽያጩ ደረሰኝ ላይ ወይም ዕቃዎቹን ወደ አገር ሲያስገባ በዲክላራሲዮን ላይ የሽያጭ ታክስ የከፈለ እና የታክስ ተመላሽ ያላገኘ መሆኑን ካረጋገጠ ፤

ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው የሽያጭ ታክስ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ታክስ ይሆናል ። ሆኖም ለእያንዳንዱ ብቁ ስለሆነ ዕቃ ተቀናሽ የሚደረገው የሽያጭ ታክስ ዕቃዎቹ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስ የሚከፈልባቸው ቢሆን ሊከፈል ከሚገባው ታክስ የበለጠ ሊሆን አይችልም ።

፮· በማናቸውም የታክስ ዘመን ውስጥ የተመዘገበው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት ተቀናሽ የሚደረግ የሽያጭ ታክስ ያለው እንደሆነ ፣ ተቀናሽ የሚደረገው የገንዘብ መጠን በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ተቀናሽ የሚደረግ ሆኖ ይቆጠራል ። ስለሆነም በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ በታክስ ዘመኑ ውስጥ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ ስለሆነ የሚቀናነስ ታክስ የተደነገገው ተፈፃሚነት ይኖረዋል ።

፯· በአቅርቦቱ ወይም ወደ አገር በገባው ዕቃ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ቢሆን ኖሮ የተከፈለው ታክስ በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ተቀናሽ የማይደረግ ከሆነ ፣ ለአቅርቦቱ የተከፈለው ሽያጭ ታክስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት ተቀናሽ አይደረግም ።

፰· የተመዘገበው ሰው አዋጁ በፀናበት ቀን በእጁ በሚገኙት ብቁ የሆኑ ዕቃዎች ላይ የከፈለው የሽያጭ ታክስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት እንዲቀናነስለት ሊጠይቅ የሚችለው አዋጁ በፀናበት ቀን ተመዝግቦ የተገኘ ከሆነ ብቻ ነው ።

፱· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የተከፈለ ታክስ እንዲቀናነስለት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ከሚያቀርበው የመጀመሪያው የታክስ ማስታወቂያ ጋር አዋጁ በፀናበት ቀን በእጁ የነበሩትን ብቁ የሆኑ ዕቃዎች ዝርዝር እና በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የሽያጭ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማቅረብ አለበት ።

፲· አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የተከፈለ የሽያጭ ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግ ያለመፈቀዱ በአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ተቀናሽ እንዲደረግ እንዳልተፈቀደ ታክስ አይቆጠርም ።

፲፩· አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ተዋዋዮች መካከል ውል የተፈፀመ እና በዚህ ውል ውስጥ ስለታክስ አከፋፈል ያልተጠቀሰ ከሆነ አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ በውሉ መሠረት በሚፈፀም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ አቅራቢው ከገዥው ሊጠይቅ ይችላል ።

፲፪· አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ የተፈረመው ውል ስለታክስ ክፍያ የማይጠቅስ ከሆነ የውሉ ዋጋ ታክስን የሚጨምር እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል ። ስለሆነም አቅራቢው ለታክሱ ክፍያ ኃላፊ ይሆናል ።

፲፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፮) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ከአቃ እና አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ፦–

ሀ) የዕቃው የባለቤትነት ስም የተዘዋወረው ፣ የዕቃው ርክክብ የተፈፀመው ወይም አገልግሎቱ የተሰጠው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ከሆነ ፣ እና

ለ) ክፍያ የተፈፀመው ወይም ደረሰኝ የተሰጠው ከተጠቀሰው ቀን ዘጠኝ ወር በፊት ከሆነ ፣

አቅርቦቱ ተፈጽሟል የሚባልበትን የሂሣብ ጊዜ ወይም የታክስ ማቀናነስ የሚፈቀድበትን ጊዜ ለመወሰን ፣ ክፍያው የተፈፀመው ወይም ደረሰኙ የተሰጠው አዋጁ በፀናበት ቀን እንደሆነ ተደርጐ ይቆጠራል ።

፲፬· የሽያጭ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የተሰጡ እንደሆነ እና ክፍያው የተፈፀመው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ባለው ፬ ወር ጊዜ ውስጥ ከሆነ በእነዚህ አገልግሎቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ አይከፈልም ።

(ii) the Authority is satisfied that sales tax has been charged to the person on a sales invoice and paid on the acquisition or import of those goods, and the sales tax has not been rebated,

the amount of the creditable sales tax shall be the amount of such taxes paid on such goods, but with respect to each item qualifying for the tax shall not exceed the amount of tax which would have been payable had the goods been subject to tax chargeable under the Proclamation.

6) If, in any tax period, a registered person has sales tax creditable under Sub-Article (5) of this Article, the amount creditable is deemed to be tax creditable under Article 21 of the Proclamation and is subject to the provisions of Article 27 of the Proclamation relating to the excess of credits over the amount of tax charged for the accounting period.

7) No credit shall be allowed under Sub-Article (5) of this Article for any sales tax paid in respect of the acquisition of any goods if the VAT imposed on a supply or import in acquisition of those goods after the effective date of the Proclamation would not be creditable under Article 21 of the Proclamation.

8) A person may claim a credit under Sub-Article (5) of this Article for sales tax paid on qualifying goods on hand on the date on which the Proclamation comes into force, only if the person is a registered person as of such date.

9) A person claiming a credit under Sub-Article (5) of this Article shall submit with the first VAT return after the tax comes into force an inventory of all qualifying goods on hand at the beginning of the first day on which the Proclamation comes into force, supported by documentary evidence of the payment of sales tax.

10) A disallowance of a credit for sales tax imposed before the date on which the Proclamation comes into force, shall not be treated as a disallowance for purposes of Article 4, Sub-Article (5) of the Proclamation.

11) Where a contract is concluded between two or more parties before the Proclamation comes into force, and no provision relating to tax is made in the contract, the supplier shall recover from the recipient, tax due on any taxable transaction made under the contract and made after the date on which the Proclamation comes into operation.

12) Where a contract concluded after the date on which the Proclamation comes into operation does not include a provision relating to tax, the contract price shall be deemed to include tax and the supplier under the contract shall account for the tax due.

13) Subject to Sub-Article (16) of this Article, if in connection with a supply of goods or services,

(a) title to goods passes, delivery of goods is made or services are rendered after the date on which the Proclamation comes into force; and

(b) payment is received or an invoice issued within nine months before that date,

for the purposes of determining the accounting period in which the supply occurs or a tax credit is allowable, the payment is treated as having been made or the invoice is treated as having been issued on the date on which the Proclamation came into force.

14) If services subject to sales tax were rendered before the date on which the Proclamation came into force and payment is made within four months after the Proclamation came into force, VAT is not imposed on the supply of the services.

፲፫· ክፍያው በተወሰነ ጊዜ ልዩነት እንዲፈፀም ማድረግ በሚያ ስችል ውል ዕቃ የተከራየ እንደሆነ ወይም የሽያጭ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች የመስጠት ተግባር አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት ተጀምሮ አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ የሚጠናቀቅ ከሆነ ፣ አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የተሰጠው አገልግሎት ዋጋ የተከፈለው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ከአራት ወራት በላይ ቆይቶ ካልሆነ በስተቀር ፣ ክፍያው የአራቱ ወር ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው ቀን ለተሰጠ አገልግሎት እንደተፈፀመ ክፍያ ተቆጥሮ አዋጁ ከተጠናቀቀ በኋላ በተሰጠው አገልግሎት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈላል ።

፲፮· በንዑስ አንቀጽ (፲፫) የተደነገገው ቢኖርም ፣ አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተፈረመ ስምምነት መሠረት የግንባታ ፣ የማምረት ወይም ሕንፃን የማስፋፋት ወይም የሲቪል ኢንጂነሪንግ ሥራ የተከናወነ እና የተከናወነው ሥራ ወደ ገዥው የተላለፈው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ከሆነ እንዲሁም አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የተከናወነው ሥራ ዋጋ በታክሱ ባለሥልጣን በፀደቀው አኳኋን የተወሰነ ከሆነ እና አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ ባለው የአቅራቢው የመጀመሪያ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሂሣብ ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን ከቀረበ ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈለው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ በተከናወነው ሥራ ዋጋ ላይ ብቻ ይሆናል ።

፲፯· አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በሚጀምር እና አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ በሚጠናቀቅ የኪራይ ውል መሠረት በተከራየ ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ አዋጁ ከፀናበት ጊዜ በፊት ላለው የኪራይ ዘመን የተከፈለው የኪራይ ሂሣብ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚከፈልበት ሂሣብ ውስጥ አይጠቃለልም ።

ክፍል ፪
ከታክሱ ነፃ ስለመሆን

፲፱· የመኖሪያ ቤት

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) ትርጉም መሠረት "የመኖሪያ ቤት" ለመኖሪያ አገልግሎት አስፈላጊ የሆነውን ከመኖሪያ ቤት ጋር የተያያዘውን ወይም የዚሁ ተቀጽላ የሆነውን ቅጥር ግቢ የሚጨምር ሲሆን ፣ ከመኖሪያ ቤት ጋር የተያያዘውን የእርሻ ቦታ አይጨምርም ። ስለሆነም ለነዋሪዎች አገልግሎት የሚውል ወደ ተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚወስድ የግቢ ውስጥ መንገድ ፣ የእግር መንገድ ፣ የመናፈሻ ሥፍራ የመኖሪያ ቤቱ አካል ሆኖ ይቆጠራል።

፪· ለሚከራይ መኖሪያ ቤት የሚውል አዲስ ወይም ያገለገለ ንብረት ለመግዛት የተመዘገበ ሰው ያወጣው ወጪ ከታክሱ ነፃ ለሆነው መኖሪያ ቤት የዋለ ከሆነ በግዥው ዋጋ ላይ የተከፈለው ታክስ እንዲቀናነስ አይፈቀድም ።

፫· አሠሪው ለተቀጣሪዎቹ በዓይነት በሚሰጠው ጥቅም መልክ የመኖሪያ ቤት የተሰጠ እንደሆነ ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለሠራተኞች በዓይነት የተሰጠውን ጥቅም አሠሪው በንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ሂደት ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንዳዋለው መቁጠር ሳይሆን ፣ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪(ሀ) መሠረት ከታክሱ ነፃ እንደሆነ መውሰድ ነው ። አሠሪው ከታክሱ ነፃ ለሆነው በዓይነት ለተሰጠው ጥቅም ባወጣው ወጪ ላይ የከፈለው ታክስ በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ በተደነገገው መሠረት ተቀናሽ እንዲሆን አይፈቀድም ።

፬· የመኖሪያ ቤት አካል የሆነ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራ መኖሪያ ቤቱን ለገዛው ሰው የተሸጠ እንደሆነ ወይም የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ የመኖሪያ ቤት ኪራይ አካል ሆኖ የተከራየ እንደሆነ ከታክሱ ነፃ ይሆናል ።

15) If goods are leased under an agreement that provides for periodic payments or if services subject to sales tax were rendered during a period that began before and ended after the Proclamation came into force, VAT is imposed on the consideration for the services rendered after the Proclamation came into force, except that to the extent the consideration for the services rendered before the Proclamation came into force is paid more than four months after the Proclamation came into force, the consideration is treated as consideration for the rendition of services on the day after the end of that four month period.

16) Notwithistanding Sub-Article (13) of this Article, if construction, manufacture or extension of building or civil engineering work is performed under a written agreement executed before the Proclamation came into force and the property is made available to the recipient after that date, VAT is imposed only on the value of work performed after that date if the value of the work on the day before the Proclamtion came into force is determined in a manner approved by the Authority and is submitted to the Authority by the end of the supplier's first VAT period after VAT comes into force.

17) If immovable property is provided under a rental agreement, for a period that commences before and ends after the date the Proclamation comes into force, the consideration for the rental shall not include the amount attributable to the period that ends before the effective date of the Proclamation.

CHAPTER 2
Exemptions

19. *Dwellings*

1) A "dwelling," defined in Article 8, Sub-Article (1)(b) of the Proclamation, includes that area surrounding or appurtenant to the dwelling that is necessary for its enjoyment, but not farm land adjacent to a dwelling. The land surrounding a dwelling complex, including the driveway, paths, gardens and landscaped grounds for the use and enjoyment of residents is part of the dwelling.

2) A registered person who purchases a new or used property for lease as a dwelling is denied tax credits for tax on any costs attributable to the exempt lease of the dwelling.

3) If an employer provides a dwelling to an employee as a fringe benefit, the exemption for the supply under Article 8, Sub-Article (2)(a) of the Proclamation takes priority over Article 4, Sub-Article (3) of the Proclamation treating fringe benefits provided to employees as supplies by the employer in the course or furtherance of a taxable activity. The employer under Article 21 of the Proclamation is denied tax credits for tax on costs attributable to the exempt fringe benefit.

4) A sale of a parking space that is part of the dwelling to the purchaser of a dwelling, or the lease of a parking space as part of a lease of a dwelling is exempt from tax.

፳. የፋይናንስ አገልግሎቶች፣

፩. በዚህ ደንብ ትርጉም የሚሸፈኑ የፋይናንስ አገልግሎቶች በግልጽ በሚታወቅ ወይም ግልጽ ባልሆነ ክፍያ የተሰጡ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) መሠረት ከታክሱ ክፍያ ነፃ ናቸው ።

፪. ከታክሱ ነፃ የተደረጉ የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ ፤

ሀ) በአበዳሪው ወይም በዋስትና ሰጪው የሚከናወን ብድርን ፣ የዱቤ ሽያጭን ወይም የብድር ዋስትናን ማስተዳደርን ጨምሮ ብድር ፣ የዱቤ ውል ወይም የብድር ዋስትናን መስጠት ፣ መደራደር ወይም በእነዚህ መንገድ ፣ ወይም

ለ) ዕዳን መሰብሰብ ወይም በውክልና መሥራትን ሳይጨምር ከገንዘብ ፣ (የገንዘብ ምንዛሪን ጨምሮ)፣ ተቀማጭ ሂሣብ ፣ ቁጠባ እና ተንቀሳቃሽ ሂሣብ ፣ ክፍያ ፣ የገንዘብ ዝውውር ፣ ዕዳ ፣ ቼክ ወይም ከሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ጋር በተያያዘ የሚከናወን እንቅስቃሴ ወይም፣

ሐ) ዱቤው በተለየ ክፍያ የተሰጠና ዕቃውን የገዛው ሰው የተለየ ክፍያ ስለመኖሩ የተገለፀለት ከሆነ በኪራይ ግዥ ወይም በግዥ ውል መሠረት የተሰጠ ዱቤ ፣ ወይም

መ) በዚህ ደንብ ከተደነገገው ሣያልፍ የኢንሹራንስ ፖሊሲ መስጠት ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲን ባለቤትነት ማስተላለፍ ወይም በዚህ ፖሊሲ ላይ የጠለፋ ዋስትና መስጠት ፣ ወይም

ሠ) የተወሰነ ጥቅም ለማስገኘት ከተቋቋመ ፈንድ ፣ ከፕሮቪደንት ፈንድ፣ ከጡረታ ፈንድ፣ በየዓመቱ፣ የተወሰነ ገንዘብ ማግኘት ከሚያስችል የጡረታ አገልግሎት ፈንድ ፣ ወይም ከጥበቃ ፈንድ ፣ ክፍያን ወይም ማናቸውንም ጥቅም ለማግኘት ከሚያስችል ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን የሚያስችልን መብት መስጠት ወይም የዚህን መብት ባለቤትነት ማስተላለፍ ፣ ወይም

ረ) ከ(ሀ) እስከ (መ) የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች አሰጣጥ ማመቻቸት፤ ወይም

ሰ) ነፃ የሕክምና አገልግሎት ለሚሰጡ ማኅበረሰቦች ወይም ለሕክምና ዕርዳታ ፈንድ የአገናኝ አገልግሎት መስጠት ፣

፫. ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚከተሉት ከዚህ በታች የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤

ሀ) «ቼክ" የፖስታ ቤት ማዛዣን፣ የገንዘብ ክፍያ ትእዛዝን፣ የመንገደኛ ቼክን ወይም ማናቸውም የፋይናንስ ተቋም አንድን ሂሣብ ዴቢት ወይም ክሬዲት እንዲያደርግ የተሰጠን ትእዛዝ (በጽሑፍ፣ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም በሌላ መንገድ) ይጨምራል።

ለ) «ገንዘብ» ማለት ለጥንታዊ ሰብሳቢ ፣ በኢንቬስት መንት እቃነት ፣ የየአገሩን ሣንቲም ለጥናት ለሚሰበሰብ ሰው ወይም በገንዘብ ልውውጥ ተግባር ሣይሆን በሌላ ዓላማ ጥቅም ላይ ከዋለው በስተቀር የማናቸውም አገር ባንክ ያወጣው ገንዘብ ወይም ሌላ የገንዘብ ሰነድ ነው፤

ሐ) «የኢንሹራንስ ፖሊሲ" ማለት ለመድን ንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠትና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፶፮/፲፱፻፹፮ መሠረት የጠቅላላ ኢንሹራንስ ንግድ ወይም የረዥም ጊዜ የኢንሹራንስ ንግድ ሥራ በመባል በሚታወቀው ፖሊሲ የሚሸፈን የኢንሹራንስ ዋስትና ነው።

መ) «የነጋዴ ቅናሽ» ማለት ለዕቃ አቅርቦት ወይም አገልግሎት ለመስጠት ተግባር ወይም ገዥው ድርጅት ለሚያስከፍለው ተመጣጣይ ክፍያ ክሬዲት ወይም ዴቢት እንዲደረግ የተጠየቀውን ሂሣብ በመቀበሉ ምክንያት ከነጋዴው ላይ የሚጠየቅ ሂሣብ ነው።

20. *Financial Services*

1) Financial services as defined in these regulations are exempt from tax under Article 8, Sub–Article (2)(b) of the Proclamation, whether provided for explicit or implicit fees.

2) The financial services exempt from tax include the following:

(a) granting, negotiating, or dealing with loans, credit, credit guarantees, or any security for money, including management of loans, credit, or credit guarantees by the grantor; or

(b) transactions concerning money (including the exchange of curency), deposit, savings, and current accounts, payments, transfers, debts, cheques, or negotiable instruments, other than debt collection and factoring; or

(c) provision of credit under a hire purchase agreement or sale of goods, but only if the credit is provided for a separate charge, and the separate charge is disclosed to the recipient of the goods; or

(d) to the extent provided in this regulation, provision, or transfer of ownership, of an insurance policy, or the provision of reinsurance in respect of any such policy; or

(e) provision, or transfer of ownership, of an interest, of an interest in a scheme whereby provision is made for the payment or granting of by a benefit fund, provident fund, pension fund, retirement annuity fund, or preservation fund; or

(f) the arranging of any of the services in (a) to (d) ; or

(g) provision of intermediation services by a buy–aid society or medical–aid fund;

3) For purposes of these regulations, the following definitions apply;

(a) ''cheque'' includes a postal order, a money order, a traveller's cheque, or any order or authorization (whether in writing, by electronic means, or otherwise) to a financial institution to credit or debit any account;

(b) ''currency'' means any bank note or other currency of any country, other than when used as a collector's piece, investment article, item of numismatic interest, or otherwese than as a medium of exchange;

(c) ''insurance policy'' means insurance covered under a policy treated as general insurance business or as long term insurance business under Proclamation No.86/1994: Licencing and Supervision of Insurance Business (the ''Insurance Proclamation'');

(d) ''merchant's discount'' means a charge made to merchants for accepting a credit or debit card as payment for the supply of goods or services, or a similar charge made by a buying organisation.

፬· በዚህ ደንብ ለፋይናንስ አገልግሎት ከተሰጠው ትርጉም በተጨማሪ ሚኒስትሩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ዝርዝር እንዲሁም ከፋይናንስ አገልግሎቶች ውስጥ ታክስ የሚከ ፈልባቸውን ፣ ከታክሱ ነፃ የሆኑትን እና በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸውን የሚያሣይ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል። ሚኒስትሩ አዳዲስ የፋይናንስ አገልግ ሎቶች በመፈጠራቸው ምክንያት ሊደረግ የሚገባውን ለውጥ ለማካተት ወይም በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱት የፋይናንስ አገልግሎቶች ባህሪ በመለወጡ ምክንያት ሊደረግ የሚገባውን ማሻሻያ ጨምሮ ማሻሻያ ሊደረግ ባቸው በሚያስፈልግ ምክንያቶች ዝርዝሩን ለማሻሻል ይችላል። በዝርዝሩ ላይ የሚደረገው ማሻሻያ የፀና የሚሆነው ማሻሻያው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

፭· በዚህ ደንብ ከታክሱ ነፃ መሆናቸው የተደነገገ የፋይ ናንስ አገልግሎቶች በተመዘገበ ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም ወይም በማናቸውም ሌላ ሰው የተሰጠ ቢሆንም ከታክሱ ነፃ ይሆናሉ።

፮· አንዳንድ አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ ከሆኑ አገልግሎቶች ጋር በተገናኘ አካኋን የተሰጡ ቢሆንም፣ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንውስ አንቀጽ ፪(ለ) መሠረት ከታክሱ ነፃ ሊሆኑ አይችሉም። ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሣይወሰኑ የዚህ ዓይነቶች አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ) የፋይናንስ አገልግቶችን ለሚሰጥ አቅራቢ ወይም የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለሚሰጥ አቅራቢ ደንበኞች የተሰጠ የሕግ፣ የሂሣብ አያያዝ እና የሰነድ አያያዝ አገልግሎት፣ ሊደርስ የሚችልን አደጋ የመገመት፣ ውል የማዋዋል እና የታክስ ውክልና አገልግሎት (የምክር አገልግሎትን ጨምሮ)፣

ለ) ለገንዘብ፣ ለሰነድ ወይም ለሌሎች ንብረቶች ጥበቃ የሚሰጥ የካዝና አገልግሎት፣

ሐ) የመረጃ ትንተና እና የደመወዝ መክፈያ ሊስት ዝግጅት አገልግሎት፣

መ) እዳ የመሰብሰብ ወይም የፋይናንስ ውክልና አገል ግሎት፣

ሠ/ የጡረታ አበል ክፍያን ፈንድ ማስተዳደርን የመሳሰሉ የአስተዳደር አገልግሎቶች፣

ረ) ባለአደራ፣ የፋይናንስ ምክር ፣ ከመሬት ጋር የተያ ያዘን ሀብት አስተዳደር የማቀድ አገልግሎት፣

ሰ/ ከፋይናንስ ሰነዶች ውጭ ካሉ ሀብቶች ጋር በተያያዘ የኪራይ ፣ የፈቃድ መስጠት እና ተመሣሣይ አገልግሎቶች።

፯· ለዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንውስ አንቀጽ ፮ አፈፃፀም የሂሣብ አያያዝ እና የሰነድ አጠባበቅ አገልግሎት፣ ስምምነት የተደረሰበትን ጉዳይ በማስፈፀም ሂደት የሚከናወን ሂሣብን የማጣራት ተግባር፣ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን በደንበኞች ሂሣብ ውስጥ የማወራረስ ፣ የደንበኞችን ሂሣብ የመያዝ እና ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶችን መስጠትን ይጨምራል።

፰· በፋይናንስ ወኪል ተይዞ የሚቆይን እዳ ጨምሮ በማና ቸውም ሁኔታ የሌላን ሰው እዳ ይዞ ማቆየት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት አይሆንም። በፋይናንስ ውክልና ወይም ከፋይናንስ ውክልና ጋር በተገናኘ አገልግሎት፣ ከሽያጭ ተግባር ጋር የተዛመደ የሂሣብ አያያዝ አገል ግሎት መስጠትን ጨምሮ እዳን ከማስመለስ ተግባር ጋር የተያያዘ አገልግሎት፣ ክስን የመከታተል ከባለእዳዎች የሚፈለግን እዳ የማስተዳደር አገልግሎት ታክሱ ይከፈል ባቸዋል።

4) In addition to the definition of financial services under these regulations, the Minister may issue a directive listing financial services and specifying their treatment as taxable, exempt, or zero–rated supplies. The Minister may modify any such list, including changes required by the introduction of new financial services or modification of the nature of the services specified in the list, with any such modification or cancellation having prospective effect only.

5) Financial services that are listed as exempt under these regulations are exempt, whether rendered by a registered bank or financial institution or by any other person.

6) Some services are not exempt under Article 8, Sub–Article (2)(b) of the Proclamation, whether or not they are rendered in connection with an exempt financial service. They include, but are not limited to the following:

(a) Legal, accounting and record package services, actuarial, notary, and tax agency services (including advisory services) when rendered to a supplier of financial services or to a customer of that supplier of financial services;

(b) Safe custody for cash, documents or other items;

(c) Data processing and payroll services;

(d) Debt collection or factoring services;

(e) Management services, such as management of a superannuating fund;

(f) Trustee, finanacial advisory, and estate planning services, and

(g) Leases, licenses, and similar arrangements relating to property other than a financial instrument.

7) For purposes of Article 20, Sub–Article (6) of these Regulations, accounting and record package services include a financial clearing system that may be part of the settlement process, the posting of financial transactions to customers' accounts the maintenance of customers' accounts, and the rendering of services ancillary to the services just described.

8) The mere acquisition of a debt is not a taxable transaction, including debt acquired by a factor. The services related to debt recovery, litigation, and the management of the recovery of the amount due from debtors are taxable, including sales accounting services under a factoring arrangement and other services related to factoring.

፱· በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ) ወደ ውጭ አገር ከሚላክ እቃ ጋር በተያያዘ የሚሰጡ የፋይናንስ አገልግሎቶች፣

ለ) ያልተመዘገበ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወደ ውጭ አገር ለሚልካቸው እቃዎች የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን እንዲችል ከተሰጠው ብድር ጋር በተያያዘ የተሰጠ የፋይናንስ አገናኝነት አገልግሎት ፣ እና

ሐ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፭ በልዩ ሁኔታ እንደሚታይ በተደነገገው ውስጥ የሚካተት ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ባንክ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ላልሆነ በውጭ አገር ለሚገኝ ሰው የባንክ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የሚጠይቀው ክፍያ፣

፲· ከታክሱ ነፃ የተደረገ ወይም በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክሱ የሚከፈልበት የፋይናንስ አገልግሎት ከዋናው አቅርቦት ጋር በተጓዳኝ የሚሰጥ ወይም የፋይናንስ አገልግሎቱ ዋንኛው አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ ስለቅይጥ አቅርቦቶች በአዋጁ አንቀጽ ፭ የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል።

፲፩· ታክስ የሚከፈልበትን (በዜሮ የማስከፈያ ልክ የሚከፈልበትን ጨምሮ) እና ከታክሱ ነፃ የሆነውን የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ የፋይናንስ ተቋሞች እና ሌሎች አገልግሎት ሰጭዎች በአዋጁ አንቀጽ ፸፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የታክስ ማቀናነስ ሊጠይቁ የሚችሉት ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ለማከናወን በገዙዋቸው (በተከራዩት ጭምር) ወይም ወደ አገር ባስገቡዋቸው ላይ ብቻ ነው።

፲፪· ተቀናሽ የሚደረግ ታክስ ከታክሱ ነፃ በሆኑ እና ታክስ በሚከፈልባቸው አቅርቦቶች መካከል ስለሚከፋፈልበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ ፸፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው በአንድ የሂሣብ ጊዜ ውስጥ ካከናወናቸው አቅርቦቶች ፺ ፐርሰንት ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች (የአዋጁ አንቀጽ ፸፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) በሆኑ የተመዘገበ ሰው ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም (ተቀናሽ የሚደረገው ሙሉው ታክስ ይሆናል)። ለዚህ አፈፃፀም አቅራቢው ታክስ የሚከፈልበትን እና ጠቅላላውን ግብይት ለማስላት ከፋይናንስ አገናኝነት አገልግሎት ውጭ ላለው አቅርቦት ጠቅላላውን አኃዝ መሠረት ማድረግ እና በፋይናንስ አገናኝነት አገልግሎት የተጣራውን የወለድ መጠን (ከወለድ ገቢ ላይ ለወለዱ የተደረገውን ወጪ መሠረት ማድረግ ይኖርበታል።

፲፫· የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው የተጨማሪ እሴት ታክስ መመሪያ የታክሱ ባለሥልጣን ተገቢ መስሎ በታየው አኳኋን ታክስ በሚከፈልበት እና ከታክሱ ነፃ በሆነው የሽያጭ እንቅስቃሴ መካከል የታክስ ማቀናነስ የሚደረግበትን ክፍፍል መወሰን እንዲችል ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል።

፲፬· በአዋጁ አንቀጽ ፸፭ መሠረት የታክስ ማቀናነሱን ክፍፍል ለማድረግ የትኛውም ዘዴ በሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም ፣ የተመዘገበው ሰው ሥራ ላይ የዋለውን ዘዴ የሚያስረዱ መረጃዎችን መያዝ አለበት። የታክሱ ባለሥልጣን የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪዎች ስለሚሰጡዋቸው የአገልግሎት ዓይነቶች ስታትስቲካዊ መረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።

፲፭· ለፋይናንስ አገልግሎቶች የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት የኢንሹራንስ ዋስትና ለማግኘት ለሚገዛ የኢንሹራንስ ፖሊስ የሚከፈለውን አረቦን ይጨምራል ።

፲፮· ከታክሱ ነፃ የሆነ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ተጠቃሚዎች ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ሽፋን ጋር በተያያዘ ለሚያገኙት አገልግሎት የሚከፍሉት አረቦን ከታክስ ነፃ የሆነ አገልግሎት ነው።

9) Zero–rated exports of financial services include:

(a) financial services rendered in connection with an export of goods;

(b) financial intermediation services rendered in connection with a loan to an unregistered, non–resident person to finance the export of goods; and

(c) fees imposed by an Ethiopian bank on banking services rendered to a non–resident who is outside Ethiopia when the banking services are rendered, if they do not come within the exceptions in Article 35 of these Regulations.

10) If an exempt or zero–rated financial service is incidental to a main supply, or if such a financial service is the main service, the rules in Article 5 of the Proclamation on mixed supplies apply.

11) Financial institutions and others providers of financial services that make both taxable (including zero–rated exports) and exempt supplies may claim tax credits under Article 21, Sub–Article (2) of the Proclamation only on purchases (including rentals) and imports used in making taxable transactions.

12) The provisions under Article 21, Sub–Article (2) of the Proclamation on the allocation of tax credits between exempt and taxable transactions do not apply (and full tax credits are allowed) to a registered person who derives more than 90 percent of the person's total supplies in an accounting period from taxable transactions (Article 21, Sub–Article (3) of the Proclamation). For this purpose, when calculating the value of the taxable and total supplies, the supplier should use gross figures for supplies other than intermediation services and use net interest amounts (interest income less interest expense) for financial intermediation services.

13) The Value Added Tax Directive to be issued by the Minister of Revenue may give the Authority discretion to determine the allocation of tax credits between taxable and exempt supplies on a bases that the Authority considers reasonable.

14) Regardless of method used to allocate tax credits under Article 21 of the Proclamation, the registered person must retain records to substantiate the method used. The Authority may require financial service providers to submit statistical data on various product lines.

15) The exemption for financial services extends to the premiums for insurance cover under an insurance policy.

16) Premiums attributable to riders attached to an insurance policy that is exempt from tax constitute exempt services if the riders are only incidental to the provision of the insurance cover.

፲፯· ከታክሱ ነፃ የሆኑ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ተጠቃሚ ለሆኑ ሰዎች ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ሽፋን ጋር ባልተ ያያዘ የሚሰጠው አገልግሎት ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ተለይቶ የሚሰጥ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ የተጣለበት ከሆነ ታክስ የሚከፈልበት አገልግሎት ይሆናል።

፲፰· ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ጋር ያልተያያዘ አገልግሎት ተጠቃሚ ከዋናው የኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር የተዛመደ ስለመሆኑ ውሣኔ የመስጠት ብቸኛ ሥልጣን ያለው የታክሱ ባለሥልጣን ነው።

፲፱· ለኢንሹራንስ ፖሊሲ የተከፈለ አረቦን ከታክሱ ነፃ ሊሆን የሚችለው በኢንሹራንስ አዋጅ መሠረት የኢን ሹራንስ ፖሊሲዎችን ለመሸጥ ፈቃድ በተሰጠው ሰው በተሸጠ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ የተከፈለ አረቦን ሲሆን ነው።

፳· የኢንሹራንስ ደላሎች/ ወኪሎች የኢንሹራንስ ፖሊስ ለደንበኞቻቸው በመሸጥ የሚያገኙት ኮሚሽን እና ሌሎች ክፍያዎች የኢንሹራንስ አገልግሎት በተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት አይሸፈኑም።

፳፩ ስለአንድ ንብረት ጥራት፣ የተሟላ መሆን ወይም የተፈለ ገውን አገልግሎት መስጠት ስለመቻሉ ለተሰጠ ዋስትና የኢንሹራንስ ሽፋን የመስጠት አገልግሎት የአንሹራንስ ፖሊሲ ሆኖ አይወሰድም።

፳፪· <u>የዋስትና ሠነዶችን ስለመሸጥ ወይም ወደአገር ስለማስገባት</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪(ሐ) ለዋስትና ሠነዶች የተሰጠው ከታክስ ነፃ የመሆን መብት የሚከተ ሉትን ያካትታል፣

ሀ) በአደራ የመያዝ አገልግሎትን ሳይጨምር አክሲ ዮኖችን፣ ስቶኮችን፣ ቦንዶችን፣ የግምጃ ቤት ሰነዶችን ወይም ሌሎች የዕዳ ወይም የሀብት ድርሻ ዋስትናዎችን ማውጣት፣ ማዘዋወር ወይም መቀበል ወይም በእነዚህ ሰነዶች መሥራት፣

ለ) ከፋይናንስ አገልግሎት ከሚመነጩ አገልግ ሎቶች፣ ከማስተላለፊያ ውሎች፣ አማራጭ ከሚሰጡ ውሎች ወይም ተመሳሳይ አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ ግብይቶች፣

ሐ) በፊደል (ሀ) ከተዘረዘሩት የዋስትና ሰነዶች ጋር የተያያዙ አማራጭ የሚሰጡ ውሎችን ወይም ዋስትናዎችን መስጠት ወይም እነዚህን ሰነዶች ከመመሥረት፣ ከማውጣት፣ ከማዘዋወር፣ ግዴታና መብትን ከማስተላለፍ ወይም ከመቀበል ወይም በእነዚህ ሰነዶች ከመሥራት ጋር የተያያዙ ግብይቶች ፣

፪· የዋስትና ሰነዶችን ለመሸጥ ውል መዋዋል ከታክሱ ነፃ ነው። ይሁን እንጂ የዋስትና ሰነዶችን ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደው የዋስትና ሰነዶችን ከመሸጥ ጋር በተያያዘ ለማስታወቂያ እና ለሕትመት የሚደረጉ ወጪዎች፣ ለሂሣብና ለሕግ ባለሙያዎች ወይም ለአማካ ሪዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎችን ለመሳሰሉ አገልግሎቶች የሚደረጉ ክፍያዎችን አይጨምርም።

፫· ለዋስትና ሰነዶች እና ለፋይናንስ አገልግሎቶች የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ዋንኛ ተግባሩ የባለአክሲዮኖችን ፣ የአባላትን ወይም የሌሎች ሰዎችን ሀብት በሥራ ላይ ማዋል ለሆነ የንግድ ሥራ ድርጅት የሚሰጠውን የአስተዳደር አገልግሎት አይጨምርም።

፬· ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡–

ሀ) "ገንዘብ" ማለት የማናቸውም አገር ማንኛውም የወረቀት ገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ሲሆን ፣ ለገቢያ ከሚውሉት በስተቀር በታሪክነት የተሰ በሰቡ የየአገሮችን ገንዘቦች እና ለኢንቬስትመንት የሚውሉ ሰነዶችን፣ አይጨምርም።

17) Services covered in riders to exempt insurance policies that are not incidental to the insurance coverage are taxable to the extent that the independent supply of those services would be taxable .

18) .The Authority shall have the sole discretion to determine whether a non–insurance rider is incidental to the main insurance policy.

19) The premium on an insurance policy is exempt only if the premium is charged on a policy issued by a person who is licenced to issue such policies under the Insurance Proclamation.

20) Commissions and other fees earned by brokers/ agents who provide insurance coverage for their customers do not come within the exemption for insurance as a financial service .

21) An insurance policy does not include insurance cover on a warranty in respect of the quality, or performance of tangible property.

21. *Supply or import of securities*

1) The exemption for securities under Article 8, Sub–Article (2)(c) of the Proclamation covers:
   (a) transactions relating to the issuance, transfer, or receipt of, or any dealing with shares, stocks, bonds, treasury bills, or other debt or equity securities, other than custody services;
   (b) transactions relating to financial derivatives, forward contracts, options, or similar arrangements, and
   (c) transactions relating to the creation, issue, transfer, assignment or receipt of, or dealing with, an option or warrant relating to securities included in (a).

2) The underwriting of the issuance of securities generally is exempt from tax. However, the exemption for underwriting services does not extend to other services obtained in connection with an underwriting, such as advertising and printing costs, accounting, legal, and advisers' fees.

3) The exemption for securities or for financial services does not include management or administrative services provided to a business whose principal activity is investing funds for shareholders, members, or other persons.

4) For purposes of this Article,
   (a) ''currency'' means any banknote or other currency of any country, other than when used as a collector's piece, investment article, or otherwise than as a medium of exchange;

ለ) "የዕዳ ዋስትና" ማለት አንድ ሰው ያለው ወይም ሊኖረው የሚችለው የገንዘብ ክፍያን የመቀበል መብት ሲሆን ፣ ቼክን፣ ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የተሰጠን የሊዝ ፣ የፈቃድ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መብት አይጨምርም።

ሐ) "የሀብት ድርሻ ዋስትና" ማለት በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት ካፒታል ላይ ያለ የድርሻ መብት ወይም ዝግ የሆነ ኮርፖሬሽን አባል የሆነ ሰው በኩባንያው ውስጥ ያለው መብት ነው።

ፀ፪· <u>ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚውል ወርቅ ወደ አገር ስለማስገባት</u>

በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ (፪) (መ) ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ወደአገር በሚገባበት ጊዜ ከታክሱ ነፃ እንደሚሆን የተደነገገው የወርቁ የጥራት ደረጃ ወይም ወደአገር በሚገባበት ጊዜ የሚኖረው ቅርፅ ከግምት ውስጥ ሳይገባ የኢትየጵያ ብሔራዊ ባንክ ራሱ የሚያስገባውን ወይም ሌሎች ሰዎች ለባንኩ ወደ አገር የሚያስገቡትን ወርቅ ይጨምራል።

ፀ፫· <u>የሃይማኖት ወይም ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪(ሠ) በተደነገገው መሠረት የሃይማኖት ወይም ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ እና በሃይማኖት ድርጅት የሚሰጡ አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ ናቸው። ስለሆነም የሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡዋቸው የአምልኮቱ ሥርዓት አካል የሆኑ አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ በተደረገው ውስጥ የሚሸፈኑ ይሆናል።

፪· የሃይማኖት ድርጅቶች ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር ተወዳዳሪ በመሆን የሚያከናውኗቸው እንቅስቃሴዎች ወይም የአምልኮቱ ሥርዓት አካል ያልሆኑ የሃይማኖት ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከታክሱ ነፃ አይሆኑም። የእነዚህ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ የሃይማኖት ድርጅቱ መመዝገብ አለበት።

፫· የአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪(ወ) መፃሕፍት እና የታተሙ ፅሑፎች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ ፈቅዷል። ስለሆነም ለመፃሕፍት እና ለታተሙ ፅሑፎች የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት የሃይማኖት ድርጅቶች ለሚያቀርቡዋቸው መፃሕፍትና የታተሙ ፅሑፎችም ተፈጻሚ ይሆናል።

፬· ዕርዳታ ሰጪው በሰጠው ዕርዳታ ምላሽ ጥቅም የማያገኝ እስከሆነ ድረስ በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚያደርገው ዕርዳታ (በሙዳየ ምፅዋት እና በመሣሠሉት) ወይም የጉልበት አገልግሎት ታክስ አይከፈልበትም።

፭· አንድ የንግድ ድርጅት በበራሪ ወረቀት ወይም በፕሮግራሞች ላይ ስሙ እንዲጠቀስለት ለሃይማኖቱ ድርጅት ዕርዳታ የሰጠ እንደሆነ፣ የሃይማኖት ድርጅቱ ከንግድ ድርጅት የተቀበለው ዕርዳታ በክፍያ የተሰጠ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ አይወሰድም። ሆኖም በበራሪ ወረቀቶች ወይም በፕሮግራም ላይ ለማስታወቂያ የተዘጋጁ ቦታዎችን የሃይማኖት ድርጅቱ የሸጠ እንደሆነ፣ ለአገልግሎቱ የተፈጸመው ክፍያ የሃይማኖት እና ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ አገልግሎት ከታክሱ ነፃ እንደሚሆኑ በተደነገገው የሚሸፈን አይሆንም።

፮· በልማት ኮሚሽን ወይም በተመሣሣይ አካል ወይም ለዚሁ ዓላማ በተቋቋመ የሥራ ክፍል ወይም ቅርንጫፍ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት የሚያከናውን የሃይማኖት ድርጅት የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሥሩ ያሉ ኮሚሽኖች፣ የሥራ ክፍሎች፣ ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ሊጠይቅ ይችላል።

(b) "debt security" means any interest in or right to be paid money that is, or is to be, owing by any person, but does not include a cheque or an interest or right that is a lease, licence or other similar arrangement in respect of immovable property; and

(c) "equity security" means any interest in or right to a share in the capital of a juristic person or the interest in a close corporation of a member thereof.

22. *Import of gold for National Bank of Ethiopia*

The exemption for the import of gold to be transferred to the National Bank of Ethiopia under Article 8, Sub–Article (2)(d) of the Proclamation applies to imports by or for the National Bank, regardless of the level of purity of the gold or the form in which it is imported.

23. *Religious or Church-related Services*

1) The supply of religious or church-related services by a religious organization is exempt under Article 8, Sub-Article (2)(e) of the Proclamation. Generally, services rendered by a religious organization that are integral to the practice of that religion come within the exemption.

2) The activities of a religious organization that compete with the private sector or that are not integral to the practice of the religion do not come within the exemption. If the value of these taxable supplies exceed the threshold under Article 16 of the Proclamation, the religious organization must register.

3) Article 8, Sub-Article (2)(p) of the proclamation exempts books and other printed material. This exemption for books applies to supplies of books or other printed material by a religious organization.

4) The donation in kind or money (such as church plate donations) or services are not subject to tax if there is no direct link between the payment and any benefit received by the donor.

5) A receipt by a religious organization from a business is not a supply for consideration if the receipt merely entitles the transferor to be mentioned in a brochure or program, but if a religious organization receives payment when it sells space in a brochure or program, the receipt is a supply for consideration that does not come within the exemption for religious or church-related services.

6) A religious organization that operates taxable activities through a development commission or similar entity or through a division or branch may apply for or be required to separately-register one or more of the commissions, divisions, or branches as provided under the Value Added Tax Minister of Revenue Directive.

፳፬· የሕክምና አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪(ረ) የሕክምና አገልግሎቶች እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት በሐኪም ትዕዛዝ ብቻ የሚሰጡ ናቸው ተብለው የተዘረዘሩት መድኃኒቶች ወደ አገር ሲገቡና በአገር ውስጥ ሲሸጡ ከታክሱ ነፃ እንደሚሆኑ ይደነጋጋል። ስለሆነም በክፍያ የተሰጠ ቢሆንም ባይሆንም ፣ ክፍያውን የፈፀመው ታካሚው ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገን ቢሆንም የሕክምና አገልግሎቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁለት ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ ከታክሱ ነፃ ይሆናል፤

ሀ) የሕክምና አገልግሎቱ የተሰጠው በታወቀ የሕክምና ተቋም ወይም የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ ወይም በሁለቱም ከሆነ፣ እና

ለ) በዚህ ደንብ መሠረት ከታክሱ ነፃ ሊሆን የሚችል አገልግሎት ከሆነ።

፪· የሕክምና አገልገሎት ከታክሱ ነፃ ሊሆን የሚችለው በታወቀ የሕክምና ተቋም የተሰጠ ሲሆን ነው። ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የታወቀ የሕክምና ተቋም የሚባለው የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ሥራውን የሚያከናውንበት ሥፍራ፣ ሆስፒታል፣ የማዋለድ አገልግሎት መስጫ ተቋምን ወይም ክሊኒክን ይጨምራል።

፫· የሕክምና አገልግሎት ከታክሱ ነፃ ሊሆን የሚችለው የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ ሲሰጥ ነው። የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ የሚባለው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መመዝገብ ያለበትና ተመዝግቦ ማረጋገጫ የተሰጠው ዶክተር፣ የባሕል ሐኪም፣ የጤና ረዳት፣ የጤና መኮንን፣ ፊዚዮቴራፒስት እና ሌሎችንም የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይጨምራል።

፬· የሕክምና አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በታወቀ የሕክምና ተቋም የተሟላ አገልግሎት (ምግብና መኝታ ጨምሮ) ያላቸው እና የሕክምና አገልግሎቱ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ ሲሠጥ ይሆናል። የሕክምና አገልግሎት የአዕምሮ ጤንነት ማሻሻልን ጨምሮ፣ የጤንነት ምርመራ፣ በሽታን ማከም፣ መከላከል፣ የጤንነት ሁኔታን ማሻሻልን የሚያካትት ነው።

፭· ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም፣ ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው በታወቀ የሕክምና ተቋም ውስጥ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ ተኝቶ ለሚታከም ወይም ለተመላላሽ ታካሚ የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት እንዲሁም ምግብ እና መኝታ፣ እንክብካቤ እና ለታካሚው በተለይ በግል የሚደረግን ጥንቃቄ፣ ተኝቶ ወይም በተመላላሽ ለሚታከመው ሕመምተኛ የዕለት ተዕለት ዕርዳታ ማድረግን ይጨምራል።

፮· ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም፣ ከታክሱ ነፃ የሆኑት የሕክምና አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ።

ሀ) የተለየ ክፍያ የማይጠየቅባቸው በሆስፒታል ወይም በክሊኒክ የሕክምናው አገልግሎት አካል ሆነው የሚሰጡ መድኃኒቶች፣

ለ) የላቦራቶሪ፣ የራጅ ወይም ሌሎች የምርመራ አገልግሎቶች፣

ሐ) የሕክምና አገልግሎት በመስጠት ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) የተዘረዘሩ የሕክምና መገልገያዎች፣

24. Medical Services and Prescription Drugs

1) Article 8, Sub-Article (2)(f) of the Proclamation exempts the rendering of medical services, and the import and supply of prescription drugs specified in the directives issued by the Minister of Health. Medical services are exempt, whether provided with or without charge and whether paid by the patient or resident or any third party, if the medical services meet two conditions:

(a) they are rendered in a qualified medical facility or by a qualified medical practitioner, or both, and

(b) they qualify as exempt medical services in this Article of the Regulations.

2) To be exempt, medical services must be rendered at a qualified medical facility. For purposes of this Article, a qualified medical facility includes the offices of a qualified medical practitioner, a hospital, maternity home, or clinic.

3) A qualified medical service is exempt if it is provided by a qualified medical practitioner. A qualified medical practitioner includes a doctor, healer, dresser, health officer, physical therapist, and other health care provider who is required to register and registered with the Ministry of Health.

4) To qualify for the exemption, medical services must consist of qualified services (including meals and accommodations) in a qualified medical facility, and must involve the rendering of medical services by a qualified medical practitioner. Medical services involve the diagnosis, treatment, prevention, or amelioration of a disease, including the promotion of mental health.

5) for purposes of Sub-Article (1) of this Article, services that qualify as exempt medical services include the services provided to a resident or patient by a qualified medical practitioner in a qualified facility, as well as meals and accommodations, nursing and personal care, and assistance with daily living activities to meet the needs of the resident or patient.

6) For purposes of Sub-Article (1) of this Article, exempt medical services include the following:

(a) medicines and drugs that are issued in a hospital or clinic for which there is no separate charge;

(b) laboratory, X-ray, or other diagnostic service;

(c) medical devices as defined in Sub-Article (7) of this Article that are provided as part of the supply of qualified medical services;

መ) አስፈላጊ የሕክምና መሣሪያዎችን እና አቅርቦቶችን ጨምሮ በኦፐራሲዮን ክፍል፣ በተለየ የሕክምና ክትትል ክፍል እና በማደንዘዣ መስጫ መሣሪያዎች መጠቀም፣

ሠ) ከታክሱ ነፃ ከሆኑ የሕክምና አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ፣የጨረር ሕክምና፣ የፊዚዮቴራፒ ወይም የኦኩፔሽናል ቴራፒ አገልግሎትን መጠቀም፣

ረ) ከታክሱ ነፃ የሆነውን የሕክምና አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዘ የሚቀርብ መኝታ እና ምግብ (ተኝተው ወይም በተመላላሽ ከሚታከሙ ሕመምተኞች በተጨማሪ ለሌሎች ሰዎች አገልግሎት ከሚሰጥ ምግብ ቤት በስተቀር)፣

ሰ) ከታክሱ ነፃ ከሆነው የሕክምና አገልግሎት ጋር በተያያዘ በሕክምና ተቋሙ ሠራተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች (ከሕክምና ውጪ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሠራተኞችን ወይም ቴክኒሺያኖችን ጨምሮ)፣

ሸ) ለአጠቃላይ የጥርስ ሕክምና እና ውበትን ለመጨመር ካልሆነ በስተቀር በሕመም፣ በአደጋ ምክንያት በተፈጠረ ጉዳት፣ባልተስተካከለ አፈጣጠር ምክንያት የሚደረግ የጥርስ፣ ወይም የአፍ ውስጥ ሕክምና፣

ቀ) የአዕምሮ መረበሽን የማከም አገልግሎት፣

፯· ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) (ሐ) አፈፃፀም የሕክምና መገልገያ ማለት በታወቀ የሕክምና ተቋም የሚቀርብ ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ የሕክምና አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዘ በሐኪም ትዕዛዝ ጥቅም ላይ የሚውል መሣሪያ ነው።

ሀ) የአተነፋፈስ ወይም የልብ ምት መቆጣጠሪያ፣ የኩላሊት ቁሻሻን ማስወገጃ መሣሪያ፣ በራሱ መመገብ የማይችል ሰው የሚገለገልበት የመመገቢያ ዕቃ ፣

ለ) የሕክምና አገልግሎት አካል ሆኖ ለበሽተኞች የሚሰጥ የታወኩ የሰውነት ክፍሎችን የሚተካ ሰው ሰራሽ የሰውነት አካል፣ የአካል ድጋፍ መሣሪያ፣

ሐ) ለታወቀ የሕክምና ተቋም የሚቀርብ የሕክምና ወይም የቀዶ ጥገና መሣሪያ ወይም እነዚህን መሣሪያዎች ተኝቶ ወይም በተመላላሽ ለሚታከም በሽተኛ ማከራየት፣

፳፭· <u>የትምህርት አገልግሎት</u>

፩· የአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ (፪) (ሠ) በትምህርት ተቋሞች የሚሰጥ የትምህርት አገልግሎት እና በመዋዕለ ሕፃናት የሚሰጥ የሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎት ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ አድርጓል። ስለሆነም ለትምህርት አገልግሎት በተለይ የሚፈፀሙ ክፍያዎች የሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ከታክሱ ነፃ ይሆናሉ።

ሀ) በዚህ ደንብ በተለይ የተመለከቱ፣

ለ) በታወቀ የትምህርት ተቋም ለተማሪዎች የሚሰጡ ከሆነ፣

፪· ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ለመሆን አገልግሎቶቹ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ዕውቅና በተሰጣቸው ተቋሞች ለተማሪዎች የተሰጡ መሆን አለባቸው።

ሀ) በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣

ለ) በሙያ ኮሌጅ እና በዩኒቨርሲቲ እና

ሐ) የጐልማሶችን ትምህርት ለማስፋፋት የተቋቋሙ ተቋሞች፣ የእጅ ሙያ ማሠልጠኛዎች፣ የልዩ ሙያ ሥልጠና መስጫዎች ወይም የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኞችን ለማሠልጠን የተቋቋሙ ተቋሞች፣

(d) the use of operating rooms, case rooms, or anesthetic facilities, including necessary equipment or supplies;

(e) the use of radiotherapy, physiotherapy, or occupational therapy facilities in rendering exempt medical services;

(f) accommodation and meals (except in a restaurant or cafeteria available to persons other than patients or residents) provided to patients or residents in the course of receiving exempt medical service;

(g) services rendered by the medical facility staff (including orderlies or technicians) in connection with exempt medical services;

(h) dental, periodontal, and endodontal services rendered in connection with a disease, trauma, or congenital deformity, but not for general dentistry or for cosmetic reasons; and

(i) psychoanalytic services.

7) For purposes of Sub-Article (6)(c) of this Article, medical devices means devices that are supplied to a resident or patient in a qualified medical facility, supplied to a qualified medical facility, or supplied on prescription in connection with the rendition of qualified medical services, including:-

(a) a respiratory or heart monitor, dialysis machine, or feeding utensil for use by an individual with a disability;

(b) a medical or surgical prosthesis or orthopedic aid provided as part of the rendition of qualified medical services; and

(c) medical or surgical equipment supplied to a qaualified medical facility, or the sale or rental of such equipment to a patient or resident.

25. Education Services

1) Article 8, Sub–Article (2)(g) of the Proclamation exempts education services rendered by educational institutions, and child care services at pre-school institutions. Qualified charges for education services are exempt if the services meet two conditions:

(a) they are specified in these regulations; and

(b) they are provided to students by a qualified educational institution.

2) To qualify for the exemption, the services must be provided to students by an accerdited:

(a) pre-primary, primary, or secondary school;

(b) technical college or university; or

(c) institution established to promote adult education, vocational training, technical education, or education or training of physically or mentally handicapped persons.

፫· በንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩት የትምህርት ተቋሞች በግል ለትርፍ በተቋቋሙ ድርጅቶች፣ ለትርፍ ባልተ ቋቋሙ ማኅበራት፣ በሃይማኖት ወይም በዕርዳታ ድርጅቶች ወይም በመንግሥት አካላት የሚካሔዱ ቢሆንም ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

፬· በንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩት የትምህርት ተቋሞች ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ዕውቅና ያገኙ ወይም አገልግሎቱን በሰጡበት ጊዜ ዕውቅና ለማግኘት በመገምገም ላይ ያሉ ከሆነ ብቻ ነው።

፭· ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ የሆኑ የትምህርት አገልግሎቶች ናቸው፤

ሀ) ዕውቅና በተሰጠው የትምህርት ተቋም ለተማሪዎች የሚሰጡ ኮርሶች፣

ለ) ዕውቅና በተሰጠው የትምህርት ተቋም የትምህርቱ ፕሮግራም አካል ሆነው ለተማሪዎች በዓይነት የሚሰጡ የምግብ ወይም ሌሎች ከአገልግሎቱ ጋር ዝምድና ያላቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች፣

ሐ) በትምህርት ተቋሙ የሚሰጡ ከሆነ የፈተና መመሪያዎች እና ፈተና የመስጠት አገልግሎቶች፣

መ) ዕውቅና ካገኘ ኮርስ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ የማስተማር ወይም የማጠናከሪያ ትምህርት አገልግሎት፣

፮· ከትምህርት ተቋሙ ጋር በሚደረግ ውል መሠረት በግል ኩባንያ ከሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት በስተቀር ተማሪዎችን ከቤታቸው ወደቅድመ 1ኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ለመውሰድ እና ወደ ቤታቸው ለመመለስ በትምህርት ተቋሙ የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት የትምህርት አገልግሎት እንደሆነ ተቆጥሮ ከታክሱ ነፃ ይሆናል።

፯· ለትምህርት አገልግሎት በተለይ የሚፈፀሙ ክፍያዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ) ለትምህርት፣ ከትምህርት ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች፤ ከትምህርት ፕሮግራም ጋር ለተያያዙ እንቅስቃሴዎች እና ለሥልጠና የሚፈፀም ክፍያ፤

ለ) ከትምህርት ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች ግዴታ ሆነው የተጣሉ ክፍያዎች ከታክሱ ነፃ የሆኑ የትምህርት አገልግሎቶች ይሆናሉ።

ሐ) የተማሪዎች ምክር ቤት ክፍያ፣ የአትሌቲክስ ክፍያ እና ለኮርስ ከመመዝገብ ጋር በተያያዘ በግድ መፈፀም ያለባቸው ክፍያዎች፤

መ) ለሪፖርት ካርድ፣ ለመፃሕፍት ቤት አገልግሎት፣ ለመታወቂያ ካርድ፣ ለመረጃ ጥበቃ እና ከትምህርት ኮርሶች ጋር በቀጥታ ለተያያዙ እና በትምህርት ተቋሙ ለሚሰጡ ሌሎች አስተዳደራዊ አገልግሎቶች የሚፈፀም ክፍያ፤

ሠ) ለኮርስ ማቴሪያሎች፣ ትምህርቱን በሚሰጠው ተቋም ለሚቀርቡ ከትምህርት ፕሮግራም ጋር ለተያያዙ ዕቃዎች ኪራይ (ለምሳሌ የሙዚቃ መሣሪያዎች ኪራይ)፣ በአመዛኙ የመዝናኛ ባህሪ ካለው በስተቀር ከትምህርት ፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ የሚደረግ ጉብኝት እና

ረ) ትምህርቱን በሚሰጠው ተቋም ለተማሪዎች የሚቀርብ የመኝታ አገልግሎት (ሆስቴልን ጨምሮ)

፰· ከትምህርት ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች የሚፈፀሙ ክፍያዎች፣ ለሕንፃ ለሜዳዎች፣ ለመፃሕፍት ቤቶች፣ ለኮምፒውተር፣ ለሣይንስ እና ለሌሎች ቤተ ሙከራዎች የሚፈፀመውን ክፍያ ይጨምራሉ።

3) An educational institution in (2) is qualified, whether it is a private school operating on a for-profit basis, or a non-profit organization, church, or charity, or a department of government.

4) An educational institution in sub-Article (2) is a qualified institution only if the institution is accredited or is being evaluated for accreditation by the accrediting agency at the time the services are rendered.

5) The following categories of services qualify as exempt education services:

(a) course of instruction provided to students at a qualified education institution;

(b) qualified meal plans, and other associated goods or services provided in kind as part of the education program of a qualified provider of education services;

(c) instruction in, or the administration of examinations, if provided by the educational institution; and

(d) instruction or tutoring related to a qualified course.

6) School bus transportation to and from pre-primary, primary, or secondary schools is an exempt education service if it is provided by the school authority, not if provided by a private company under contract with the school authority.

7) Qualified charges for exempt education services include:

(a) charges for tuition, facilities, and curriculum-related activities and instruction;

(b) compulsory levies for facilities are part of a supply of exempt education services;

(c) student council fees, athletic fees, and other manadatory fees related to course registration;

(d) charges for reports, library services, identity cards, record keeping and other administrative services provided by the educational institution and directly related to the supply of education courses;

(e) charges for course materials, the rental of curriculum-related goods by the supplier of the education (e.g., the rental of musical instruments), field trips directly related to the curriculum if not predominantly recreational; and

(f) student accommodations (including hostels) supplied by the supplier of the education.

8) Qualified facility charges include charges for buildings, grounds, libraries, and computer, science and other laboratories.

፱· ከታክሱ ነፃ የተደረገው የትምህርት አገልግሎት የሚከተሉትን አይጨምርም፤

ሀ) ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ የሚያስገኙ ፕሮግራሞች አካል ካልሆኑ በስተቀር ስፖርት፣ ጨዋታዎች፣ የቪዲዮ ቀረፃ ወይም የፎቶግራፍ ወይም የጊዜ ማሳለፊያ ወይም የመዝናኛ ተግባራት፤

ለ) የግል ዕውቀትን ለማዳበር ታስበው ለሚሰጡ ፎቶግራፍን በፎቶግራፍ ማስቀመጫ የማስቀመጥ፣ የምግብ ዝግጅት እና የግል ሁኔታን ለማሻሻል የሚሰጡ ኮርሶች፤

ሐ) የትምህርት ፕሮግራም አካል ያልሆነ የሙዚቃ ትምህርት፤

፲· ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የኃይማኖት ትምህርት እየተከታተሉ የኃይማኖት አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ተማሪዎች ሆነው ይቆጠራሉ።

፲፩· በንዑስ አንቀጽ (፬) ከታክሱ ነፃ ከተደረጉት አገልግሎቶች በተጨማሪ በቅድመ–አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛ ደረጃ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጡ ከታክሱ ነፃ የሆኑ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ) የልዩ ትምህርት ኮርሶችን ጨምሮ መሠረታዊ ትምህርቶች፤

ለ) በት/ቤቶች ለሚሰጡ የቅድመ–አንደኛ ደረጃ ወይም ከትምህርት በኋላ ለሚካሄዱ ፕሮግራሞች የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

ሐ) በት/ቤቶች የሙዚቃ መሣሪያዎች ወይም የስፖርት ዕቃዎች ለመጠቀም የሚፈፀሙ ክፍያዎች፤

መ) የትምህርቱ ፕሮግራም አካል ሆነው በተማሪዎች ወይም በመምህራኖቻቸው የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ እና

ሠ) ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚካሔዱ ጫወታዎች፣ ዳንሶች፣ የመስክ ጉዞዎች ወይም በሌሎች በት/ቤት ውስጥ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ ለመሆን የሚፈፅሙዋቸው ክፍያዎች፤

፲፪· ከታክሱ ነፃ የሆኑ በዩኒቨርሲቲዎች ወይም በቴክኒክ ኮሌጆች የሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ተማሪው የዲግሪ ወይም የዲፕሎማ ፕሮግራሞችን የሚከታተል ቢሆንም ባይሆንም ለዲግሪ ወይም ለዲፕሎማ የሚያበቁ ኮርሶችን በተልዕኮ ትምህርት መስጠትን ይጨምራል።

፲፫· ከታክሱ ነፃ የሆነው የጐልማሶች ትምህርት፣ የሙያ ሥልጠና፣ የቴክኒክ ትምህርት እና ለአካል ወይም ለአዕምሮ ጉዳተኞች የሚሰጥ ትምህርት እና ሥልጠና የሚከተሉት ይጨምራል፤

ሀ) ለዲግሪ ወይም ለዲፕሎማ የሚያበቁ ለጎልማሶች የሚሰጡ ኮርሶች ወይም በኮርሱ ተሳታፊ የሚሆኑ ተማሪዎችን ከቅጥር ጋር የተያያዘ ክሕሎት ለማሳደግ ያስችላሉ የተባሉ ኮርሶች፤

ለ) የተማሪዎችን የሙያ ክሕሎት ለማሻሻል ወይም ለማሳደግ የሚያስችሉ በሙያ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ኮርሶች፤

ሐ) አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ የመንግሥት መ/ቤት የተሰጠውን የሙያ ወይም የንግድ ዕውቅና ወይም ስያሜ ለማቆየት ወይም ደረጃውን ለማሻሻል የሚያስችሉ ኮርሶች፤

መ) ዕውቅና ወይም ስያሜ ለማግኘት በሚሰጡ ኮርሶች ወይም ፕሮግራሞች ፈተና ወይም የምስክር ወረቀት መስጠት፤

፲፬· ኮርሶች ከቅጥር ጋር የተያያዘውን ክህሎት ያሳድጋሉ የሚባለው የኮርሱ ዓላማ ተማሪዎች የሚቀስሙትን ክህሎት በትክክል የሚገልጽ እና ተማሪዎች የቀሰሙትን ክህሎት ለመዝናኛ፣ ለትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ፣ ለኪነጥበብ ወይም ለባህል ሳይሆን በተቀጠሩበት መ/ቤት፣ በሙያ ወይም በንግድ ሥራ መስክ ያውሉታል የሚል ግምት ካለ ነው።

9) The exemption for education services does not cover the following education courses:

(a) course in sports, games, video recording or photography or other hobbies or recreational pursuits, unless they are part of a degree-or diploma-granting program;

(b) course, such as picture framing, cooking, and personal investment, that are designed to improve knowledge for personal purposes; and

(c) music lessons that are not part of a school curriculum.

10) Religious workers receiving education are treated as students for purposes of this Article of the Regulations.

11) In addition to services exempt under (4), exempt education services rendered by a pre-primary, primary, or secondary school include -

(a) basic instruction, including special education courses;

(b) fees or charges for a pre-school or after-school program operated by the school;

(c) charges for the use of school musical instruments or sports equipment;

(d) services rendered by students or their teachers as part of the instructional program; and

(e) charges for students to attend a school play, dance, field trip, or other school-sanctioned activity primary for the students.

12) Exempt education services rendered by a university of technical college include courses, including correspondence courses, that qualify for credit toward a degree or diploma, whether or not the student is pursuing a degree or diploma program.

13) The education exemption for adult education, vocational training, technical education, and education or training of physically or mentally handicapped persons includes charges for :

(a) adult education courses leading to a degree or diploma or courses that are liekely to enhance employment-related skills of the students enrolled in the courses;

(b) courses of study at a vocational school that develop or enhance a student's occupational skills;

(c) courses leading to, or to maintain or upgrade, a professional or trade accreditation or designation recognized by the appropriate government accrediting agency; and

(d) a certificate or examination in a course or program for accrediation or designation.

14) Courses enhance employment-related skills if the course objectives specify those skills that students will acquire, and there is a reasonable expectation that the skills taught will be used by the students in their employment, businesses, professions, or trades, rather than for recreational, hobby, artistic, or cultural purposes.

፲፭· ለትምህርት አገልግሎቶች የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት የሚከተሉትን አይጨምርም፤

ሀ) የትምህርት ተቋሙ የትምህርት አገልግሎት መስጫዎችን ከት/ቤቱ ውጪ ላሉ ቡድኖች ያከራየ እንደሆነ፤

ለ) ለአጠቃላዩ ኅብረተሰብ ክፍት በሆነ ሁኔታ በት/ቤቱ በሚካሄዱ የአትሌቲክስ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ የሚያስችል ክፍያ መጠየቅ፤

ሐ) በትምህርት ተቋሙ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሣንቲም የሚሠሩ ማሽኖችን በማስቀመጥ የሚገኝ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ፤ እና

መ) የትምህርት ቤቱን አርማ የመሳሰሉ ከትምህርት ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ማቴሪያሎች በመሸጥ የሚገኝ ገቢ፤

፳፮· ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ አቅርቦቶችና በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸውን መልሶ ለማቋቋም ከአገር ውስጥ የሚገዙና ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች

፩· ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ አቅርቦቶች ከታክስ ነፃ እንደሚሆኑ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሸ) የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው በበጎ አድራጎት ድርጅትነት የተመዘገቡ ድርጅቶች ለዚሁ ዓላማ ወደ አገር ለሚያስገቧቸውና በአገር ውስጥ ለሚገዟቸው ዕቃዎች ነው።

፪· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሸ) ከታክሱ ነፃ ስለመሆን የተደነገገው ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ በመድረሱ ምክንያት የአደጋ መከላከያና ዝግጁነት ኮሚሽን ባደረገው የዕርዳታ ጥሪ መሠረት ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎችን ይጨምራል።

፳፯· ውሃ

በፋብሪካ ታሽጎ ከሚሸጥ ውሃ በስተቀር የውሃ አቅርቦት በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ቀ) በተደነገገው መሠረት ከታክሱ ነፃ ነው።

፳፰· በሕግ ወይም በስምምነት ከታክሱ ነፃ የተደረጉ ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (በ) በሕግ ወይም በስምምነት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ከሌሎች ታክሶች ነፃ የተደረጉ ድርጅቶች ተቋሞችና ፕሮጀክቶች ወደ አገር ለሚያስገቧቸው ዕቃዎች ከታክስ ነፃ እንደሚሆኑ ተደንግጓል።

፪· ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ በአዋጅ የተፈቀደ፤ ወይም በአዋጅ በተሰጠ ሥልጣን መሠረት በደንብ ወይም በመመሪያ ከታክስ ነፃ የሆኑት ከታክሱ በሕግ ነፃ የተደረጉ በሚለው ተካተው ነፃ ይሆናሉ።

፫· በስምምነት ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተፈፃሚ የሚሆነው በመንግሥት ወይም በመንግሥት በተሰጠ ፈቃድ መሠረት በተደረጉ ስምምነቶች ነፃ የተደረገ ሲሆን ብቻ ነው።

፬· በስምምነት ከታክሱ ነፃ የተረጉ የሚለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይጨምራል።

ሀ) በኢትዮጵያ መንግሥትና በማናቸውም ድርጅት ወይም በማናቸውም አገር መንግሥት መካከል የተደረገ የቴክኒክ ትብብር ወይም የሰብዓዊ ዕርዳታ ስምምነት፤

ለ) በዲፕሎማቲክ ልዩ መብቶችና ጥቅሞች ደንብ የተፈቀደ፤

ሐ) የኢትዮጵያ ሕግ አካል በሆነ ዓለም አቀፍ ስምምነት፤

መ) ማናቸውም ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት ሌላ የባለብዙ ወገን ስምምነት፤

15) The exemption for education services does not include;

(a) the rental of facilities by an educational institution to an outside group;

(b) the sale of admission to school athletic events open to the general public;

(c) commissions and other fees received from the placement of coin-operated machines on the institution's property; and

(d) the sale of non-course material, such as items containing the school logo.

26. Supplies of Humanitarian Aid, and Imports of Goods for Rehabilitation after Natural Disasters, Industrial Accidents, and Catastrophes

1) The exemption for supplies of humanitarian aid under Article 8, Sub-Article (2)(h) of the Proclamation applies to goods imported or purchased locally by organizations registered as humanitarian organizations, for such purposes.

2) The exemption under Article 8, Sub-Article (2)(h) of the Proclamation covers the import of goods or purchase of goods locally in connection with an announcement or declaration of a natural disaster, industrial accident, or catastrophe by the Disaster Prevention and Rehabilitation Commission.

27. Water

A supply of water is exempt from tax under Article 8, Sub-Article (2)(i) of the Proclamation, unless it is processed in a factory.

28. Imports Exempt by Law or Agreement

1) Article 8, Sub-Article (2)(j) of the Proclamation exempts imports of goods by the government, organizations, institutions or projects only to the extent that they are exempt from duties and other import taxes by law or by agreement.

2) An exemption by law covers an exemption for certain imports granted by a Proclamation or, when specifically delegated by a Proclamation, granted by a Regulation or Directive.

3) An exemption by agreement covers tax exemptions for certain imports of goods only if the agreement is entered into by the government or the agreement is entered into with permission granted by the government.

4) The exemption by agreement includes an exemption provided under;

(a) a technical assistance or humanitarian assistance agreement entered into between the Government of any country;

(b) the Diplomatic Immunities and Privileges Registrations,

(c) an international convention having the force of law in Ethiopia;

(d) any other multilateral agreement to which Ethiopia is a party;

፳፱· ትራንስፖርት

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ቸ) ለትራንስ ፖርት አገልግሎት የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት በማናቸውም ዓይነት ትራንስፖርት ሰዎችን ወይም ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የሚፈፀምን ክፍያ ያካትታል።

፪· ዕቃዎችን ወይም መንገደኞችን በዓለም አቀፍ ትራንስ ፖርት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የማጓጓዝ እንቅስቃሴ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ቸ) መሠረት ከታክሱ ነፃ በሆነው ሥር የሚወድቅ ከሆነ፤ ይህ እንቅ ስቃሴ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ይሆናል።

፴· ፈቃድ ለማግኘት የሚፈጸሙ ክፍያዎች

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ነ) ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ የሚፈፀም ክፍያ ከታክስ ነፃ እንደሚሆን የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው በመንግሥት አካላት ለሚሰጡ ፈቃዶች ብቻ ነው።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸውን መብቶች ለመጠቀም ወይም ለሌሎች በንብረት መጠቀም ለመሳሰሉ መብቶች በግል ተዋዋዮች የሚሰጡ ፈቃዶችን አይጨምርም።

፴፩· በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ለ) ከቀረጥ ነፃ ስለተደረጉ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች

በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ኘ) በተደነገገው መሠረት በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ቀረጥ ነፃ የተደረጉ ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደው ተፈጻሚ የሚሆነው በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ለ) ለተዘረዘሩት እና በደንቡ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ከቀረጥ ነፃ ለሆኑ ዕቃዎች ብቻ ነው።

፴፪· አካል ጉዳተኞች የሚሠሩባቸው ድርጅቶች

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (አ) የተደነገገው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተፈጻሚ የሚሆነው የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኞችን ቀጥረው የሚያሠሩ ድርጅቶች ለሚያቀርቧቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ብቻ ነው።

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ከሠራተ ኞቻቸው መካከል ፷ በመቶ አካል ጉዳተኞች መሆናቸው የተረጋገጠ ድርጅቶች ናቸው። ከሠራተኞች መካከል ፷ በመቶ አካል ጉዳተኞች መሆናቸው የሚረጋገጠው ባለፉት ፲፪ ወራት ከነበሩት ጠቅላላ ሠራተኞች መካከል የአካል ጉዳተኞችን ቁጥር በመቶኛ በመውሰድ ነው። ይሁን እንጂ ድርጅቱ ሥራ ከጀመረ ከ፲፪ ወራት በታች ከሆነ ድርጅቱ ሥራ ላይ በቆየባቸው ጊዜያት ያሉት ሠራተኞች ብዛት በመለኪያነት ያገለግላል።

፴፫· መጻሕፍት

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ወ) ከታክሱ ነፃ ስለመሆን የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው ለታተሙ መፃሕፍት እና መፅሐፍትን ወቅታዊ ለማድረግ ለሚወጡ እትሞች ነው። ይህ ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ለታተሙ ወይም ላልታተሙ የኃይማኖት ጽሑፎች ጭምር ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፪· የአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ወ) ለዓይነሥውራን ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች በተለይ የተዘጋጁ ተናጋሪ መፃሕፍት ወደአገር በሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ጊዜ ተፈፃሚ ከሚሆን በስተቀር ለሌሎች ተናጋሪ መፃሕፍት ተፈጻሚ አይሆንም።

29. *Transport*

1) The exemption for transport services under Article 8, Sub-Article (2)(1) of the Proclamation is a broad exemption covering the charges imposed for the transport of passengers or freight by any mode of transport.

2) If a transaction involving the international transport of goods or passengers qualifies for exemption under Article 8, Sub-Article (2) (l) of the Proclamation, Article 8, Sub-Article (4) treats the transaction as zero-rated.

30. *Permits and Licenses*

1) The exemption for permits and license fees under Article 8, Sub-Article (2)(m) of the Proclamation is limited to fees charged for permits and licenses issued by a government agency.

2) The exemption in (1) does not apply to licenses of intangibles and other licenses or permits, such as the right to use property, granted by private parties.

31. *Imports Exempt under Schedule 2"B" of Customs Tariffs Regulations.*

The exemption granted under Article 8, Sub-Article (2)(n) of the Proclamation for imports of goods exempt under Schedule 2 of the Customs Tariffs Regulations is limited to the exemptions granted under part (B) of Schedule 2 of Customs Tariffs Regulations and under Directives issued pursuant to those Regulations.

32. *Workshops for Disabled*

1) The exemption under Article 8, Sub-Article (2)(o) of the Proclamation applies to goods sold and services rendered by workshops employing physically or mentally disabled individuals.

2) To qualify for the exemption under Sub-Article above more than 60 per cent of the workshop's employees must be disabled. The 60 per cent threshold is measured by the number of disabled and total employees in the previous 12 months, except that if the workshop has been in existence for less than 12 months, then the threshold is measured for the number of months the workshop has been in existence.

33. *Books and other Printed Materials*

1) The exemption under Article 8, Sub-Article (2)(p) of the Proclamation applies to a printed book or an update of a book. The exemption applies to a bound or unbound printed version of scripture of any religion.

2) The exemption for books generally does not apply to an audio recording that is a spoken reading of a printed book, except that the exemption under Article 8, Sub-Article (2)(p) of the Proclamation applies to import and supplies of talking books (in cassettes or other forms of recording) specifically designed for the blind or severely handicapped.

ክፍል ፫
በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች

፴፬ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ መሆኑን ስለማስረዳት

የተመዘገበው ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ለአቅርቦቱ ዜሮ የማስከፈያ ልክን ተፈጻሚ ያደረገ ከሆነ፣ ዜሮ የማስከፈያ ልክን ለመጠቀም ብቁ የሚያደርጉትን እና በታክሱ ባለሥልጣን ተቀባይነት ያላቸውን የሰነድ መረጃዎች ተቀብሎ መያዝ አለበት።

፴፭ ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን ወደውጭ ስለመላክ

፩· በዚህ አንቀጽ ውስጥ፦

ሀ) "ዕቃዎች የሚላኩበት አገር" ማለት ከኢትዮጵያ ውጪ ያለ ማናቸውም አገር ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝን ማናቸውንም ቦታ ይጨምራል። ሆኖም የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚላኩበት አገር ተብሎ አይወሰድም ብሎ የሚሰይመውን የተለየ አገር ወይም ግዛት አይጨምርም።

ለ) "ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የተላኩ" ማለት የተመዘገበ ሰው በሽያጭ ወይም በዱቤ ሽያጭ ስምምነት መሠረት ከሚያቀርባቸው የሚንቀሣቀሱ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ፦

፩· በተመዘገበው ሰው ተቀባዩ ባለበት አገር በሚገኝ አድራሻ የተላከ ለመሆኑ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ተቀባይነት ባለው የሰነድ መረጃ የተረጋገጠ፣

፪· አውሮፕላኑ ዕቃዎቹ ወደሚላኩበት አገር የሚጓዝ ከሆነ የተመዘገበው ሰው ወደውጭ አገር ለሚሄድ አውሮፕላን ባለቤት ወይም ተከራይ ዕቃዎቹን ሲያስረክብ ወይም ዕቃዎቹ በአውሮፕላኑ ውስጥ በጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ፣

፪· የሚከተሉት ወደውጭ አገር የሚላኩ አቅርቦቶች በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሀ) መሠረት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው ናቸው፣

ሀ) አቅራቢው ወደውጭ እንዲላኩ በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ዲክላራሲዮን የሞላባቸው እና በአቅራቢያው ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር የተላኩ ዕቃዎች፣

ለ) በአቅራቢያው ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር የተላኩ ስለመሆኑ የታክሱ ባለሥልጣን ማረጋገጫ ያገኘ ባቸው ዕቃዎች፣

ሐ) አቅርቦቱ በተፈፀመ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበሩ እና አቅራቢው በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ ወደአገር መልሶ የማያስገባቸው ዕቃዎች፣

መ) ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የተሰጠ አገልግሎት

(i) አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ የነበረ ተንቀሣቃሽ ንብረት፣

(ii) በጉምሩክ አዋጅ ምዕራፍ ፭ መሠረት በጊዜያዊነት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች፣

(iii) "ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር ለተላኩ ዕቃዎች" በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈኑ በፊደል (ለ) (፩) ወይም (ለ) (፪) የተመለከቱ ዕቃዎች አቅርቦት፣

ሠ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) (ii) ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው ዕቃዎች ጥገና፣ ዕድሣት፣ ማሻሻያ ወይም ሕክምና በማድረግ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎች እና

(i) በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የተለጠፉ፣ የተገጠሙ፣ ከእነዚሁ ጋር የተያያዙ ወይም የእነዚሁ አካል የሆኑ ዕቃዎች፣

(ii) በጥገና በዕድሣት፣ በማሻሻያ ወይም በማስተካከያ ሥራዎች ሂደት ጥቅም ላይ የማይውሉ ወይም ዋጋ የማይኖራቸው የፍጆታ ዕቃዎች፣

CHAPTER 3
Supplies Subject to Zero Tax Rate

34. *Substantiation of Zero Rating*

Where a registered person has applied the rate of zero percent to a supply under these regulations, the registered person shall obtain and retain such documentary proof acceptable to the Authority substantiating the person's entitlement to apply the zero rate to the supply.

35. *Export of Goods or Services*

1) In this Article-

(a) "export country" means any country other than Ethiopia and includes any place which is not situated in Ethiopia, but does not include any specific country or territory that the Minister of Finance and Economic Development may by Directive designate as one that is not an export country;

(b) "exported from Ethiopia" in relation to any movable goods supplied by any registered person under a sale or credit agreement, means-

1) consigned or delivered by the registered person to the recipient at an address in an export country as evidenced by documentary proof acceptable to the Authority; or

2) delivered by the registered person to the owner or charter of any foreign-going aircraft when such aircraft is going to a destination in an export country and such goods are for use or consumption in such aircraft, as the case may be;

2) The following supplies are zero-rated exports within Article 7, Sub-Article (2)(a) of the Proclamation:

(a) a supply of goods where the supplier has entered the goods for export, pursuant to the Customs Proclamation, and the goods have been exported from Ethiopia by the supplier;

(b) a supply of goods where the Authority is satisfied that the goods have been exported from Ethiopia by the supplier;

(c) a supply of goods where the goods are not situated in Ethiopia at the time of supply and are not to be entered into Ethiopia for home consumption pursuant to the Customs Proclamation by the supplier of the goods;

(d) a supply of services directly in respect of

(i) movable property situated outside Ethiopia at the time the services are rendered;

(ii) goods temporarily imported into Ethiopia under Chapter 5 of the Customs Proclamation; or

(iii) a supply of goods referred to in (a) or (b) of the definition of "exported from Ethiopia",

(e) a supply of goods in the course of repairing, renovating, modifying, or treating any goods to which Sub-Article (2)(d)(ii) of this Article applies and the goods supplied

(i) are worled into, affixed to, attached to, or otherwise form part of those other goods; or

(ii) being consumable goods, become unusable or worthless as a direct result of being used in that repair, renovation, modification, or treatment process;

ረ) ከኢትዮጵያ ውጪ ካለ መሬት ወይም በዚሁ መሬት ላይ ማናቸውንም ማሻሻያ ከማድረግ ጋር በቀጥታ በተያያዘ ሁኔታ የተሰጠ አገልግሎት፣

ሰ) "ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር ለተላኩ ዕቃዎች" በተሰጠው ትርጉም ከሚሸፈኑ በፊደል ለ((i) ወይም ለ(፪) ከተመለከቱ ዕቃዎች አቅርቦት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

ሸ) ከኢትዮጵያ ውጪ የተሰጡ አገልግሎቶች፣

ቀ) ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አገልግሎቶች በስተቀር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ እና አገልግሎት በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ ለነበረ ሰው የተሰጡ አገልግሎቶች፣

(i) በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ጋር በቀጥታ የሚያያዙ አገልግሎቶች፣

(ii) አገልግሎቱ ከተሰጠ በኋላ የሚንቀሣቀሰው ንብረት ከኢትዮጵያ ውጪ ካልተላከ በስተቀር አገልግሎቱ በተሰጠ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለ የሚንቀሣቀስ ንብረት ጋር በቀጥታ በተያያዘ ሁኔታ የተሰጠ አገልግሎት፣

(iii) በኢትዮጵያ ውስጥ ማናቸውንም ታክስ የሚከፈልበትን አገልግሎት ለመስጠት መታቀብን የሚጨምሩ አገልግሎቶች፣

(iv) ኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት የሚያካሂድን ሰው ያለማወክን የሚጨምሩ አገልግሎቶች፣

በ) የሚከተሉትን የሚጨምሩ አገልግሎቶች፡–

(i) በአዕምሮአዊ ሀብት መብቶች ከኢትዮጵያ ውጪ ለመጠቀም ማስመዝገብ፣ መከታተል፣ መስጠት፣ መጠበቅ፣ ማዘዋወር፣ ማስተላለፍ፣ ፈቃድ መስጠት ወይም ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ፣

(ii) በንዑስ አንቀጽ ((i) የተመለከተውን አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆኑ ተጓዳኝ አገልግሎቶች፣

(iii) የአዕምሮአዊ ሀብት መብቶችን ከኢትዮጵያ ውጪ በሙሉ ወይም በከፊል በጥቅም ላይ ከማዋል ለመታቀብ ግዴታ የሚያስገቡ ሁኔታዎችን መቀበል፣

፫· በዚህ አንቀጽ መሠረት ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክሱ እንዲከፈልባቸው ለማድረግ ዕቃዎቹ በሚወጡበት ወደብ የሚገኘው ላኪ ዕቃዎችን ለይቶ ማሳየት እና በባለሥልጣኑ የሚጠየቀውን የሰነድ መረጃ ማቅረብ አለበት።

፬· በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪(ሀ) ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክሱ እንደሚከፈልባቸው የተደነገገው ለውጭ ገበያ የሚልከው አቅራቢ መልሶ ወደአገር ላስገባቸው ወይም ለሚያስገባቸው ዕቃዎች ተፈጻሚ አይሆንም።

፭· የተመዘገበ ሻጭ ዕቃዎቹን ወደውጭ አገር ለሚልክ የተመዘገበ ገዥ፣ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶችን ጨምሮ ማናቸውንም ግዙፋዊ ሀልዎት ያላቸውን (የግል ንብረቶች)የአልኮል መጠጦችን፣ ቢራ ወይም ትምባሆ ሳይጨምር) የሸጠ እንደሆነ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ዕቃዎቹ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግባቸው ይሆናል፡–

ሀ) ለሽያጭ የቀረቡት ዕቃዎች ዓይነት እና አግባብነት እስካለው ድረስ የገዥውን መደበኛ የንግድ ሥራ አካሄድ ባህርይ ጨምሮ የእያንዳንዱን የግዥ ሁኔታ መሠረት በማድረግ እንቅስቃሴው ይወሰዳል ተብሎ በሚገመት አጭር ጊዜ ውስጥ ገዥው የተረከባቸውን ንብረቶች ለውጭ ገበያ የላከ ከሆነ፣

(f) a supply of services directly in connection with land, or any improvement thereto, situated outside Ethiopia;

(g) a supply of services to a non-resident person who is not a registered person comprising the arranging for the person of a supply of goods referred to in (a) and (b) of the definition of "exported from Ethiopia";

(h) a supply of services physically rendered else where than in Ethiopia;

(i) a supply of services to a non-resident person who is outside Ethiopia at the time the services are supplied, other than a supply of services;

(i) directly in connection with immovable property situated in Ethiopia;

(ii) directly in connection with movable property situated in Ethiopia at the time the services are supplied unless the movable property is exported from Ethiopia subsequent to the supply of services;

(iii) comprising the refraining from undertaking any taxable activityin Ethiopia; or

(iv) comprising the tolerating of another person undertaking any taxable activityin Ethiopia;

(j) a supply of services comprising-

(i) the filing, prosecution, granting, maintenance, transfer, assignment, licensing, or enforcement of intellectual property rights for use outside Ethiopia;

(ii) incidental services necessary for the supply of services referred to in (i) above; or

(iii) the acceptance by any person of an obligation to refrain from pursuing or exercising in whole or part, intellectual property rights for use outside Ethiopia;

3) To obtain zero rating for the export of goods and related services under this Article, the exporter, at the port of exit, must identify the goods and present documentary proof required by the Authority.

4) Zero-rating for exports under Article 7, Sub-Article (2) (a) of the Proclamation does not apply to any export of goods which have been or will be re-imported to Ethiopia by the supplier for export.

5) A supply of tangible personal property (including natural resources, but not including spirits, beer or tobacco) made by a registered person to a registered recipient who will export the goods in zero-rated, if all of the following conditions are met:

(a) the recipient exports the property as soon after the goods are delivered to the recipient as is reasonable having regard to the facts of each situation, including the type of goods involved and, where applicable, the normal business practice of the recipient;

ለ) ላኪው ዕቃዎቹን የገዛው ወደውጭ አገር ከመላካቸው በፊት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወይም በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ ወይም በገበያ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ካልሆነ፣

ሐ) አስፈላጊነቱ አጥጋቢ በሆነ ምክንያት የተደገፈ ወይም ዕቃውን ከማጓጓዝ ተግባር ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ካልሆነ በስተቀር ዕቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ተጨማሪ የምርት ሂደት እንዲያልፉ፣ ባህሪያቸው እንዲቀየር ወይም ማሻሻያ እዲደረግባቸው ካልተ ደረገ፣

መ) አቅራቢው ዕቃዎቹ በገዥው ወደውጭ አገር የተላኩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ፣

፮· ለንዑስ አንቀጽ (፭) አፈጻጸም፣

ሀ) ገዥው ዕቃዎቹን ወደውጭ አገር ለመላክ ያቀደ እና በእርግጠኝነት የሚልካቸው መሆን አለበት።

ለ) የገዛቸውን ዕቃዎች ወደውጭ አገር ለሚልክ የተመዘገበ ሰው ለመሸጥ ላቀደ ሰው የሚፈጸም ሽያጭ ወደውጭ አገር ለሚልክ ሰው እንደተፈጸመ አቅርቦት አይቆጠርም፣

ሐ) ዕቃዎች በምርት ሂደት እንዲያልፉ፣ ባህሪያቸው እንዲ ቀየር ወይም ማሻሻያ እንዲደረግባቸው ማድረግ ከተፈጥ ሮአዊ ለውጥ በስተቀር በዕቃዎቹ ላይ አካላዊ ወይም ኬሚካላዊ ለውጥ ማስከተል የሚችልን አዘገጃጀት፣ አያያዝ ወይም ሌላ ተግባር ይጨምራል። ሆኖም የዕቃ ቆጠራ፣ ማቀዝቀዝ፣ በመጋዘን ማስቀመጥ ወደውጭ ለመላክ ማሸግ ወይም እንደገና ማሸግ፣ በሚላክበት አካኋን ምልክት ማድረግ፣ ወደውጭ በሚላክበት ሣጥን መክተት፣ መጫን ወይም ማውረድ የመሳሰሉ አገልግሎ ቶችን አይጨምርም።

መ) ዕቃዎች ወደውጭ አገር የተላኩ መሆኑን የሚያረጋ ግጠው ማስረጃ በታክስ ባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባለው ቅጽ የተዘጋጀ ዕቃው ወደ ውጭ መላኩን የሚያረጋግጥ በገዥው የሚቀርብ የምስክር ወረቀት መሆን አለበት።

፴፮ የዕቃዎች ወይም የመንገደኞች ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት

፩· በዚህ አንቀጽ ውስጥ

ሀ) "ለትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ የሆነ አገልግሎት" ማለት ዕቃዎችን የመጫን እና የማውረድ አገል ግሎት፣ ጭነቱን የማሰር ወይም ደኅንነቱን የማረጋገጥ አገልግሎት፣ ጭነቱን የመመርመር አገልግሎት፣ የጉምሩክ ሰነዶችን የማዘጋጀት፣ ኮንቴይነር የመጫንና የማውረድ አገልግሎት፣ የተጓጓዘውን ወይም ለመጓጓዝ የተዘጋጀውን ዕቃ በመጋዘን የማስ ቀመጥ አገልግሎት ነው።

ለ) "ወደውጭ አገር የሚበር አውሮፕላን" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በዋነኛነት በኢትዮጵያ በሚገኝ አውሮ ፕላን ማረፊያ እና ዕቃዎች ወደውጭ አገር በሚላ ኩበት አውሮፕላን ማረፊያ መካከል ወይም ዕቃዎች ወደውጭ አገር በሚላኩባቸው አውሮፕላን ማረፊ ያዎች ከአንዱ ወደሌላው ሰዎችን እና ዕቃዎችን በክፍያ በማጓጓዝ ተግባር ላይ የተሠማራ አውሮፕላን ነው።

ሐ) "ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት" ማለት

፩) ለትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ ከሆኑ አገልግሎቶች በስተቀር ሰዎችን እና ዕቃዎችን፦

(i) ጉዞው ወይም የጉዞው ከፊል የኢትዮጵያን ግዛት አቋርጦ የሚሄድ ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ ወጪ ከሆነ አንድ ቦታ ከኢትዮጵያ ውጪ ወደሆነ ሌላ ቦታ፣

(ii) ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኝ ቦታ፣

(iii) በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ ቦታ ከኢትዮጵያ ውጭ ወደሚገኝ ቦታ፣

በየብስ፣ በውሃ፣ በአየር የማጓጓዝ አገልግሎት፣

(b) the recipient has not acquired the goods for consumption, use or supply in Ethiopia before exportation;

(c) the goods must not be further processed, transformed or altered in Ethiopia, except to the extent reasonably necessary or incidental to its transportation, after delivery and before its exportation; and

(d) the supplier must maintain evidence satisfactory to the Authority of exportation of the goods by the recipient.

6) For purposes of Sub-Article (5),–

(a) the recipient must intend to export the goods and must in fact export the goods;

(b) a supply to a recipient who intends to sell to a registered person who will export the goods is not treated as a supply to a recipient who will export the goods;

(c) processing, transformation, or alteration includes preparation, handling or other activity that causes a physical or chemical change in the property, other than natural growth, but generally does not include services such as inventory-taking, refrigeration, warehousing, export packing or repacking, export labeling, export crating, loading or unloading; and

(d) evidence of exportation can be satisfied with documents satisfactory to the Authority, such as an export certificate from the recipient of the goods in a form acceptable to the Authority.

36. *International Transport of Goods or Passengers*

1) In this Article–

(a) "ancillary transport services" means stevedoring services, lashing and securing services, cargo inspection services, preparation of customs documentation, container handling services, and storage of transported goods or goods to be transported;

(b) "foreign-going aircraft" means any aircraft engaged in the transportation for reward of passengers or goods wholly or mainly on flights between airports in Ethiopia and airports in export countries or between airports in export countries;

(c) "international transport services" means:

1. the services, other than ancillary transport services, of transporting passengers or goods by land, water, or air.

(i) from a place outside Ethiopia to another place outside Ethiopia where the transport or part of the transport is across the territory of Ethiopia;

(ii) from a place outside Ethiopia to a place in Ethiopia; or

(iii) from a place in Ethiopia to a place outside Ehiopia;

፪· ጉዞው በአውሮፕላን የሚፈፀም እና በዓለም ዐቀፍ የሲቪል አቪየሽን ኮንቬንሽን አንቀጽ ፰ "ለዓለም ዐቀፍ ማጓጓዣ" በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈን እስከሆነ ድረስ መንገደኞችን በኢትዮጵያ ውስጥ ካለ አንድ ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ ማጓጓዝ፣

፫· አገልግሎቱ በዚህ ትርጉም ፊደል "ሀ" የተዘረዘሩት አገልግሎቶች አካል በመሆን በአንድ አገልግሎት ሰጪ የሚሰጥ እስከሆነ ድረስ ለትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ የሆነ አገልግሎቶችን ጨምሮ ዕቃዎችን በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ በማጓጓዝ የሚሰጥ አገልግሎት፣ ወይም

፬· በዚህ ትርጉም ከፊደል (ሀ) እስከ (ሐ) የተመለከቱት ተፈጻሚ ለሚሆኑባቸው፣ የመድን አገልግሎት፣ የመድን፣ የመንገደኞች እና የዕቃ ማጓጓዝ አገልግሎቶችን የማመቻቸት አገልግሎት።

፪· ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አቅርቦቶች በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) በተደነገገው መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግባቸዋል፣

ሀ) ዕቃዎቹ በተላኩበት የውጭ አገር ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ በኪራይ ውል እና በቻርተር ውል መሠረት ዕቃዎችን ማቅረብ፣

ለ) አውሮፕላኑ ከኢትዮጵያ ውጭ ወደሆነ አገር የሚበር እና ዕቃዎቹ በአውሮፕላን ውስጥ ለፍጆታ ወይም ጥቅም ላይ የሚውሉ እስከሆነ ድረስ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚጓዝ አውሮፕላን ባለቤት ወይም ተከራይ ዕቃዎችን ማቅረብ፣

ሐ) ዓለም ዐቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፣

መ) ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚጓዝ አውሮፕላን የጥገና፣ የፅዳት ወይም የሙሉ ዕድሣት አገልግሎት መስጠት፣

ሠ) ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች በወኪል ወይም በሌላ ሰው አማካይነት ሳይሆን በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው በቀጥታ መስጠት፣

(i) ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚጓዝ አውሮፕላን በኢትዮጵያ ውስጥ ባለበት ጊዜ የሚሰጥ የማስተናገድ፣ የማብረር፣ የማዳን፣ የመጐተት አገልግሎት፣

(ii) ከኢትዮጵያ ውጭ የሚጓዝን አውሮፕላን ሥራ ላይ ከማዋል ወይም ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ አገልግሎት መስጠት፣

ረ) ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያካትት አገልግሎት በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው መስጠት፡—

(i) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) ወይም (ሠ) ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን አገልግሎቶች፣

(ii) ለትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ የሆኑ አገልግሎቶችን ጨምሮ ዕቃዎችን በኢትዮጵያ ውስጥ የማጓጓዝ አገልግሎት፣

ሰ) በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ያልተመዘገበ ሰው ለሚያካሒደው የባቡር ትራንስፖርት የሚሰጥ የጥገና እና የዕድሣት፣ የፅዳት አገልግሎት፣

፴፯· <u>ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለሚቀርብ ወርቅ</u>

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግበት ሲሆን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አገልግሎት እንዲውል ወደአገር የሚገባ ወርቅ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) መሠረት ከታክሱ ነፃ ነው።

2) the services of transporting passengers from a place in Ethiopia is to another place in Ethiopia to the extent that the transport is by aircraft and constitutes "international carriage" as defined in Article 8 of the Convention on International Civil Aviation.

3) the services, including any ancillary transport services, of transporting goods from a place in Ethiopia to another place in Ethiopia to the extent that those services are supplied by the same supplier as part of the supply of services to which (a) of this definition applies; or

4) the services of insuring or the arranging of the insurance or the arranging of the transport of passengers of goods to which (a) to (c) of this definition applies;

2. The following supplies are zero-rated supplies within Article 7, sub-Article (2)(b) of the Proclamation

(a) a supply of the goods under a rental agreement, or agreement for chartering, where the goods are used exclusively in an export country;

(b) a supply of goods delivered to the owner or charterer of a foreign-going aircraft when the aircraft is flying to a destination in an export country and the goods are to be used international transport services;

(c) a supply of international transport services;

(d) a supply of services directly in respect of the repair, maintenance, cleaning or reconditioning of a foreign-going aircraft;

(e) a supply services directly to a non-resident person not being a registered person, otherwise than through an agent or other person;

(i) comprising the handling, pilotage, salvage, or towage of any foreign-going aircraft while situtated in Ethiopia; or

(ii) provided in connection with the operation or management of any foreign-going aircraft;

(f) a supply of services to a non-resident person who is not a registered person comprising the arranging for the person of-

(i) a supply of services to which sub-Article (2)(d) or (e) of this Article applies; or

(ii) the transport of goods, including ancillary transport services, within Ethiopia;

(g) a supply of services comprising the repair, maintenance, cleaning, or reconditioning of a railway train operated by a non-resident person who is not a registered person.

37. *Supply of Gold to the National Bank of Ethiopia*

A supply of gold to the Nationàl Bank of Ethiopia is zero-rated under Article 7, Sub-Article (2)(c) of the Proclamation, and the import of gold to be transferred to the Nationl Bank exempt under Article 8, Sub-Article (2)(d) of the Proclamation.

፴፰· በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝን ድርጅት ስለማስተላለፍ

፩· አንድ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ድርጅት የተላለፈ እንደሆነ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ወይም የንግድ ሥራውን ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር እንደተከናወነ አቅርቦት እንደሚቆጠር በአዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተደንግጓል። ስለሆነም የማስተላለፉ ተግባር በአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፲) እና አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) የተዘረዘሩትን መለኪያዎች የሚያሟላ ከሆነ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግበታል። በአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) በተዘረዘሩት ሁኔታዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በተከናወነው የማስተላለፍ ተግባር የዜሮ ማስከፈያ ልክ ተጠቃሚ እንዲሆን ከተደረገ፣ የማስተላለፉ ተግባር በመንቀሳቀስ ላይ ያለውን ድርጅት ለገዛው ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።

፪· የዜሮ ማስከፈያ ልክ ተጠቃሚ ለመሆን ተዋዋይ ወገኖች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው።

ሀ) ግብይቱ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝን ድርጅት ከአንድ የተመዘገበ ሰው ወደሌላ የተመዘገበ ሰው የማስተላለፍ ተግባር መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

ለ) የማስተላለፍ ተግባር የተፈፀመ መሆኑን የሚገልጽ በአስተላለፈው እና በተላለፈለት ሰው የተፈረመበት ማስታወቂያ ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት።

ሐ) ማስታወቂያው የማስተላለፉ ተግባር በተፈፀመ በ፳፩ ቀን ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን ሊደርስ ይገባል።

መ) ማስታወቂያው ስለአቅርቦቱ መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን የሚዘረዝር መሆን አለበት።

፫· በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት ሊባል የሚችለው ራሱን ችሎ ሊሠራ የሚችልና ገቢ የሚያመነጭ ፣ ማስተላለፉ ከተፈፀመ በኋላ በእርግጠኝነት ያለማቋረጥ የሚንቀሳቀስ እና ወደፊትም ሊንቀሳቀስ የሚችል ሲሆን ነው። ሆኖም ተግባራዊ እንቅስቃሴ የማያደርግ ለወደፊት ይሠራል ተብሎ የሚታሰብ የንግድ ሥራ ሊሆን አይችልም።

፬· የተላለፈው የንግድ ሥራ አትራፊ ባይሆንም ወይም የከሰረ በመሆኑ ምክንያት ለሂሣብ አጣሪዎች፣ ለአስተዳዳሪዎች፣ ለባለአደራዎች ወይም የከሰረን ሰው ንብረት እንዲያጣራ ለሚሾም ለማናቸውም ሌላ ሰው በመተላለፍ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ሆኖ ይወሰዳል።

፭· በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት በማስተላለፍ ተግባር ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ድርጊቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በፀናበት ቀን ወይም ከዚህ ቀን በኋላ የተፈፀመ ከሆነ ብቻ ነው።

፮· በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት የማስተላለፍ ተግባር በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) በተደነገገው ዜሮ የማስከፈያ ልክ ሊካተት የሚችለው በመንቀሳቀስ ላይ ያለን የንግድ ሥራ ከሽርክና ማኅበር በሕግ የሰውነት መብት ወደተሰጠው ኩባንያ መለወጥን የመሳሰለ የሕግ አቋም ለውጥ ማድረግ ወይም የንግድ ሥራውን አካሔድ ቅርፅ መቀየር ከሆነ ነው።

፯· የንግድ ሥራው ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ እስከቻለ ድረስ የተላለፈለት ሰው ገቢ የሚያመነጨውን እንቅስቃሴ ራሱ እንዲያካሂድ መደረጉ አስፈላጊ አይሆንም።

፰· የእርሻ መሬትን ማስተላለፍ በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት ማስተላለፍ ተደርጐ አይወሰድም። ሆኖም ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ እስከታች ድረስ የግጦሽ መሬትን ከመሣሪያዎቹ እና ከከብቶቹ ጋር የማስተላለፍ ተግባር በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት ማስተላለፍ ይሆናል።

38. *Transfer of a Going Concern*

1) The transfer of all or portion of a taxable activity as a going concern is a supply in the course or furtherance of the taxable activity under Article 4, Sub-Article (9) of the Proclamation. If the tranfer meets the requirements of Article 4, Sub-Article (10) and Article 7, Sub-Article (2)(d) of the Proclamation, the transfer can be zero-rated. In appropriate cases described in Article 4, Sub-Article (11), a portion or the entire transfer that is zero-rated to the supplier may be treated as a taxable transaction to the person acquiring the going concern.

2) To obtain zero-rating, the parties must comply with the following requirements:

(a) The transfer must be of a going concern between registered persons;

(b) A notice of the transfer must be submitted in writing and signed by the transferor and transferee;

(c) The notice must be furnished to the Authority within 21 days after the transfer takes place; and

(d) The notice must include the essential details of the supply.

3) A going concern is an income-producing activity capable of separate operation that is in fact operational and capable of being carried on without interruption after the transfer, but not a dormant or prospective business.

4) A transfer can be of a going concern even if the transferred business in not profitable, or is being transferred to a liquidator, receiver, trustee in bankruptcy, or other persons appointed upon the insolvency of registered person.

5) the transfer is zero-rated only if it taks place on or after the effective date of the VAT.

6) A transfer of a going concern comes within the zero rating of Article 7, Sub-Article (2) (d) of the Proclamation if the transfer is to a person with no previous interest in the business, or is a a transfer of an existing business involving only a change of legal entity or form of doing business, such as from a partnership to an incorporated company.

7) It is not necessary for the transferee to operate the particular income-producing activity acquired, so long as it is capable of separate operation.

8) The supply of farmland alone is not a supply of a going concern if it can be separately operated.

፱/ በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ድርጅት የማስተላለፍ ተግባር በእርግ ጠኝነት የተፈፀመ ቢሆንም፣ አስተላላፊው እና የተላለፈለት ሰው የተመዘገቡ ካልሆነ እና በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት አቅርቦት የተፈፀመ ሆኖ እንዲቆጠር በመጠየቅ በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) መሠረት ሁለቱም የፈረ ሙበት ማስታወቂያ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ አይቻልም።

፲/ ማስታወቂያ የሚቀርብበት የሯጯ ቀን ጊዜ የሚወሰነው በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ የተመለከተውን አቅርቦቱ ተፈፀመ የሚባልበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ ነው።

፲፩/ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት የተላለፈለት ሰው አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ፣ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ለአቅርቦቱ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የማስተላለፉ ተግባር በተፈፀመበት ቀን የተመዘገበ እንደሆነ ነው።

፲፪/ ተዋዋይ ወገኖች ተፈላጊውን ማስታወቂያ ያቀረቡ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) በተደነገገው መሠረት የማስተላለፉ ተግባር ለዜሮ የማስከፈያ ልክ ብቁ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ፣ ለአቅርቦቱ የተፈፀመው ክፍያ የተጨማሪ እሴት ታክስን የማይጨምር እንደሆነ ይቆጠራል። በመሆኑም የማስ ተላለፉ ተግባር ታክስ ይከፈልበታል፣ የተላለፈለትም ሰው በአዋጁ በተፈቀደው መጠን የታክስ ማቀናነስ እንዲደረግለት ሊጠይቅ ይችላል።

፲፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለታክሱ ባለሥልጣን የሚቀርበው ማስታወቂያ የተላለፉትን ንብረቶች የተሟላ ዝርዝር፣ የእያንዳ ንዱን የተላለፈ ንብረት የገበያ ዋጋ፣ አስተላላፊው የሚያካሒ ደውን የንግድ ሥራ ባህሪ፣ ንብረቱ የተላለፈለት ሰው በንብረቱ የሚያካሂደውን የንግድ ሥራ ዓይነት፣ አስተላላፊው በተላ ለፉት ንብረቶች የንግድ ሥራ ሲያካሂድ የቆየበትን ጊዜ ልክ የሚጨምር መረጃ መያዝ አለበት። የታክሱ ባለሥልጣን ከአስተላላፊው ወይም ከተላለፈለት ሰው ወይም ከሁለቱም ተጨማሪ መረጃ ሊጠይቅ ይችላል።

፲፬/ አስተላላፊው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘውን ድርጅት በማስተ ላለፉ ምክንያት ምዝገባው እንዲሠረዝ ያደረገ እንደሆነ፣ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ድርጅት አካል ሆነው ያልተላለፉ ዕቃዎች አስተላላፊው በገበያ ዋጋ ያቀረባቸው ዕቃዎች ሆነው ይቆጠራሉ። ሆኖም ይህ ድንጋጌ አስተላላፊው በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የታክስ ማቀናነስ በማያገኝባቸው ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

፲፭/ አስተላላፊው እና የተላለፈለት ሰው በጋራ ፈርመው በሚያቀ ርቡት ማመልከቻ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጭምር እንዲተላለፉ ሊጠይቁ ይችላሉ። ሆኖም የታክሱ ባለሥልጣን ጥያቄውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ብቸኛ ሥልጣን አለው።

፲፮/ በንዑስ አንቀጽ (፲፭) መሠረት የሚቀርበው ጥያቄ በታክሱ ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ፡-

ሀ/ አስተላላፊው ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ለተላለፈለት ሰው መስጠት ያለበት ሲሆን፣ የተላለፈለትም ሰው እነዚህን ሰነዶች በአዋጁ አንቀጽ ፴፯ እስከተመለከተው የጊዜ ገደብ ድረስ ይዞ ማቆየት አለበት።

ለ/ አስተላላፊው የንግድ ሥራው ባለቤት ሆኖ በቆየበት ጊዜ ውስጥ የሚፈለገውን ማናቸውንም የተጨማሪ እሴት ታክስ ዕዳ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች እንዲከፍሉ የሕግ ግዴታ አለባቸው።

9) Unless the transferor and transferee both are registered persons and both sign and file in a timely manner to treat the transfer as a supply of a going concern as required under Article 7, Sub-Article (2)(d) of the Proclamtion, the transfer is not zero-rated, even if in fact it is a transfer of a going concern.

10) The 21-day period within which the notice must be filed is determined under the time of supply rules in Article 11 of the Proclamation.

11) If the transferee previously was not a registered person, the supply can qualify for zero rating only if the transferee is registered by the date the transfer takes place.

12) If the parties file the required notice and the transfer does not qualify as a zero-rated supply of a going concern under Article 7, Sub-Article (2)(d) of the Proclamtion, the consideration charged for the supply is treated as being exclusive of VAT, the transfer is subject to tax, and the transferee can claim a tax credit to the extent allowable under the Proclamation.

13) The notice to the Authority required under this Article must include a complete list of the assets transferred, the market value of each asset transferred, the nature of the business conducted by the transferror and the business to be conducted by the transferee with the acquired assets, and the length of time the transferor's business has been operated with the assets transferred. The Authority may require additional information from the transferor or transferee, or both.

14) If the transferor cancels its registration as part of the transfer of a going concern, then goods not transferred as part of the going concern generally constitute a supply of the goods by the trasnsferor at their market values, except that this rule does not apply to goods for which the transferor has not been allowed a tax credit under Article 21 of the Proclamation.

15) The transferor and transferee, upon written application signed by both, may request a transfer of taxpayer identification number and certificate of registration, and the Authority has the sole discretion to grant or deny the request.

16) If the application under (7) is approved,-

(a) the transferor must transfer VAT records to the transferee, and the transferee must retain those records for the time required for the retention of records under Article 37 of the Proclamtion; and

(b) both parties are legally obliged to pay any VAT liability incurred while the transferor owned the business.

፴፱· መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የገቢዎች ሚኒስትር ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚረዱ መመሪያ ዎችን ለማውጣት ይችላል።

፵· ደንቡ የሚፀናበት ቀን

ይህ ደንብ አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

39. *Directives*

The Minister of Revenue may issue directives for the proper implementation of these Regulations.

40. *Effective Date*

These Regulations shall come into force as of the date the Proclamation comes into force.

Done at Addis Ababa this 31st day of December, 2002.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE